# رد المنكرات والشبهات
## بأدلة القرآن والإنجيل والتوراة

إعداد
**قمر حسين**

# ስህተትን መመለስ
## ኦሪት ወጌልና ቁር አንን በመጥቀስ

አዘጋጅ
**ቀመር ሁሴን**

الأمهرية

سلطانة
Sultanah

# ለሕቶትን መመለስ

## ኦሪትና ወንጌልን በመጥቀስ

አዘጋጅ
ቀመር ሑሴን

2ኛ እትም 1996
አዲስ አበባ

بسم الله الرحمن الرحيم

**ከአንድ ዓመት በፊት ተጽፋ ለንባብ የበቃችው "ስህተትን መመለስ" የተፈለገ ውን መልዕክት ከማስተላለፏ በላይ ከአንባቢያን ዘንድ ጥሩ ውዴታን አትርፋ ለች። በዚሁ መሠረት ጠያቂዋ እየጨመረ በመምጣቱ በውስጧ የነበሩ ትናንሽ የቃላት ግድፈቶች ታርሞና አዳዲስና ወሳኝ ነገሮችን አካታ ብቅ ብላለች። በሌላ በኩል ጽሑፏ በዐረብኛ በእንግሊዝኛና በኦሮምኛ ቋንቋዎች በቅርብ ጊዜ አሳትመን ለማሠራጨት ዝግጅቱን እያጠናቀቅን ነው።**

**መርከዝ ደዕዋ**

## ከአንባቢያን አስተያየት በጥቂቱ

**ጽሑፏን ደጋግሜ በትኩረት አንብቢያለሁ። በተለይ የሴቶች ጉዳይና የስግደት አቅጣጫን በተመለከተ በእስልምና ላይ በደብልጥ "full confidence" እንዲኖረኝ በልቤ ውስጥ ትልቅ ሃብት ትቷል። ፀሐፊውን በጣም በጣም እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቡበከርና አ/ፈታህ -ከሻሸመኔ።**

**ጽሑፏን ከማንበቤም በላይ ከፀሐፊው ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበረኝ። እጅግ ፀጣም ጠቃሚና ወሳኝ ነገሮችን በውስጧ ይዛለች። በተለይ አማኞች መርዝ ጠጥተው አይሞቱም የምትለዋን ግጥም (ማርቆስ 16:16) ምን ጊዜም አነባታለሁ። ለፀሐፊው ኸይር ጀዛእ አላህ ይከፈለውና በክርስትና ሃይማኖት ከኔ ጋር ስትኖር የነበረች ባለቤቴ ሰልማለች -አልሐምዱሊላሂ ረቢልዓለሚን።**

**ዶ/ር በረከት -ከአዲስ አበባ።**

***በአሁኑ ሰዓት በጥቃቅን ጥቅማ ጥቅሞች እየተገፉ በሰፊው እየተካሄደ ያለውን የንጽጽራዊ ሃይማኖት ትምህርትና ደዕዋ ለማጥፋትና በኛም ሕይወት ላይ አደጋ ለመጣል እየደከሙ ስላሉ አንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች በቀጣይ ጽሑፌ ላይ አላህ ካለ ስለማንነታቸው ሳልገልጽላችሁ አላልፍም።***

**ከአዘጋጁ**

---


**የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።**

جميع حقوق محفوظة للمؤلف

*All Rights Reserved*

**© 2003/1996**


---

| ተ.ቁ | ማውጫ | ገጽ |
|---|---|---|
| | **ርዕስ** | |
| 1 | መቅድም | 4 |
| 2 | መግቢያ | 6 |
| 3 | የፈጣሪ ሥልጣንና ደረጃው | 7 |
| 4 | የፈጣሪ ሥልጣንና የኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ገደብ | 10 |
| 5 | ኢየሱስ ከአላህ ተልከው መጡ ወይስ በራሳቸው ፍላጎትና ችሎታ? | 16 |
| 6 | ኢየሱስ ብቻ የእግዚአብሔር ልጅ ተባሉ ወይስ እኛም? | 18 |
| 7 | ጳውሎስ ማነው ? | 19 |
| 8 | ኢየሱስ ስለ ፈጣሪያቸው የተናገሩት ቃል | 22 |
| 9 | ያለፉት ነቢያትና የኢስላም ጸሎት ሲነጻጸር | 25 |
| 10 | የጀናባ (በግብረ ሥጋ ግንኙነት የረከሰ ሰው) ትጥበት | 25 |
| 11 | ስግደት (ሶላት) | 26 |
| 12 | ኢየሱስ | 26 |
| 13 | መንፈስ ቅዱስ | 26 |
| 14 | እግዚአብሔር (አብ) | 27 |
| 15 | ቂብላ (የስግደት አቅጣጫ) | 28 |
| 16 | የአሰጋገድ ሥርዓት | 30 |
| 17 | የሴቶች ገዲታና መብት በእምነት | 30 |
| 18 | ነቢዩ ሙሐመድ ብቻ ተዋጉ ወይስ ሌሎችም ነቢያት? | 34 |
| 19 | እውነተኛው አምላክ ማነው? ባሕሪውስ? | 35 |
| 20 | መልስ የሚሹ ጥያቄዎች | 39 |
| 21 | የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ባጭሩ ሲብራራ | 41 |
| 22 | ማን ይሞክር (ሥነ-ግጥም) | 42 |
| 23 | እንግባ ቶሎ (ሥነ-ግጥም ) | 44 |
| 24 | ትዝብት (ሥነ-ግጥም) | 45 |

# መቅድም

ከፍተኛ ምሥጋና የምድርና የሰማይ ፈጣሪ ለሆነው፣ ከጉንዳን ጀምሮ እስከ ትልቁ ዐርሽ፣ ከጠጠር ጀምሮ እስከ ትልቁ ተራራ፣ ከውሃ ጠብታ እስከ ትልቁ ባሕር፣ ባጠቃላይ የዓለማት ጌታ ለሆነው አላህ ይድረሰው። ሶላትና ሰላም ለዓለም ሁሉ መልዕክተኛ ለሆኑት ነቢያችን ﷺ ይውረድ።

በመቀጠል መላው አንባቢያን ሆይ! ይህችን አጭር መልዕክት በእርጋታ አንብቡልኝ። መልዕክቴ ግን ለሙስሊም ብቻ አይደለም። ለክርስቲያን ወገኖቼ ጭምር ነውና ያንብቡልኝ። የሰው ዘር ሆይ! ብዙ ሃብት ማካበት ከአላህ እሳት አያድንም። የአማልክት መብዛት ከአንድ አላህ አያድንም። በቃላት የረዘመ ምላስና እውነት የሌለበት ቅልጥፍናም ከቀብር ጭንቅ አያድንም።

የጎሣ መብዛትና የጡንቻ መፈርጠም ከአላህ ቁጣ ቀርቶ ከዝንብ ዘረፋ አያድንም። የድምጽ ማማር፣ የቤዝ ጊታር፣ የከራርና የደውል መብዛት፣ በሰይጣን አጃቢነት ለጊዜው ደስታን ይስጠን እንጂ በጭፈራ የሚገባ (የሚሰጥ) ርካሽ ጀነት የለምና አንታለል። የአላህ ዕቃ (ጀነት) ውድ ነው። ስለዚህ ወንድሞቼ ሁላችንም የአዳምና የሔዋን ልጆች ነን። ስለዚህ "እንጨት አትደገፉ ሲወድቅ ትወድቃላችሁ፤ ብርን አትደገፉ ሲያልቅ ታፍራላችሁ፣ ትደበቃላችሁ፤ ሰውን አትመኩ ሲሰቀል ሲገረፍ ታፍራላችሁ፣ የእርጉም ዘመዶች ትባላላችሁ።"

ኦሪት ዘዳግም 21፥22 በመስቀል ላይ የተሰቀለ ሁሉ የተረገመ ነው ይላልና። ስለዚህ በማርቆስ 12፥29 ኢየሱስ እንዳለው የትእዛዛት ሁሉ ትልቁ ፊተኛይቱ ትእዛዝ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹም ሐሳብህ መውደድና በእሱ ብቻ መመካት ስለሆነ በእርሱ ብቻ ተመካ።

ጉልበትህም ለእርሱ ብቻ ይንበርከክ፣ ትንቢተ ኢሣያስ 45፥23 «ጉልበትህ ሁሉ ለእግዚአብሔር ይንበርከክ» ይላልና። «የሚደክመውን ሰው አምላክ አትበለው። አምላክህ አይደክመውምና፣» ትንቢተ

ኢሳይያስ 40፥28 ይመልከቱ እግዚአብሔር አይደክምምና። ዮሐንስ ወንጌል 4፥6 ይመልከቱ ኢየሱስ ደክሞ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ ይላልና። የቱ ይሻላል? ምርጫውን ለርስዎ ትቻለሁ።

ስለዚህ የሰው ልጅ ሆይ! አላህ ዓለም ሁሉ ሊገበረክክለት ይገባዋልና፣ ከእርሱም የበለጠ ባለሥልጣን የለምና፣ ብትመከው የሚያድን ነውና፣ ብትለምነው የሚቸር ነውና፣ ስትታመም ከጎንህ ነውና፣ የቂያማ (የትንሣዔ) ቀን ንጉሥ ነውና፣ ከእርሱም በላጭ የለምና፣ ድካምና እንቅልፍ አያዳገተውምና፣ በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ሐሳብህ አላህን ውደድ።

ይህችን አጭር መልዕክት ለአዳም ዘር ሁሉ የጻፍኩኝ ኢትዮጵያዊው ወንድማችሁ ፈቂር ስሆን፣ አላህ ሥራዬን ለሚዛን እንዲያበቃት አንባቢያን ዱዓእ እንዲያደርጉልኝ እጠይቃለሁ።

ይህን መጽሐፍ ታትሞ ለሙስሊሙ ኅብረተሰብ እንዲዳረስ በከፍተኛ ውጣ ውረድ ሳይለዩኝ፣ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ የገፋፉኝና በሞራልና በማቴሪያል የረዱኝን የአኼራ ወንድሞች የአላህ እዝነትና ምሕረት አይለያቸው።

በተለይ ለናዝሬቱ የአኼራ ወንድሞቼና ለባለቤቶቻቸው ሙስሊሙ ኅህብረተሰብ ዱዓእ እንዲያደርጉላቸው እጠይቃለሁ።

ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለደችው ባለቤቴ ወ/ሮ ሐና ዝሜ ከጎኔ በመሆን ስለረዳችኝ አላህ ይውደዳት።

ሥራዬ እዩልኝ (ሪያእ) ኖርበት አላህ ፊት እዋረዳለሁ የሚል ስጋትም ስላለብኝ የሙስሊም ዱዓእ እንዳይለየኝ አደራዬ የጠበቀ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ንባብ ለተቀየመኝ ሁሉ ተናጋሪ አላህ የሚያነጋገ ረውን ያህል ስለሚናገር ለአላህ ብላችሁ ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እማፀናችኋለሁ! ቸር ያሰማን!

# መግቢያ

እግዚአብሔር የሚለው የአማርኛው ቃል የአምላክን ሥልጣን የሚገድብ መስሎ ስለተቀመጠ አላህ የሚለውን ለዚህ ጽሑፍ እንጠቀማለን። ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በስተቀር።

የአላህ ሥልጣን ከዚህ እስከዚህ ተብሎ ገደብ የማይጣልበት፣ ለተፈጠሩትና በኋላም ለሚፈጠሩ በአጠቃላይ በሰማያትም ይሁን በምድር ላይ ከእርሱ የሚበልጥ እንደሌለ ሙስሊሙም ይሁን ክርስቲያኑ መቀበል ያለበት ሐቅ ነው። የዚህ ጽሑፍ ትኩረትም የአላህን ትልቅነት ማሳወቅና የኢየሱስን አምላክነት ግልጽ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ማስተባበል ይሆናል።

የሚያሳዝነው ግን 'አውቆ ያንቀላፋን ቢጠሩት አይሰማም' እንደሚባለው ተረት፣ እያዩና እየሰሙ ዝም ማለቱ ነው። አንገት ለምን ተፈጠረ? አዙሮ ለማየት የሚለውን ትርጉም ያሰጠ ነውና 1ኛ ተሰሎንቄ 5፥21 'ሁሉንም ፈትኑ መልካሙን ያዙ' የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልም በአመንን ባዮች ዘንድ ብዙ ስለማያገለግል እንዲተገብሩት ለማስተማር መጣር ይኖርብናል። የዓለማችን አብዛኛው ሰው እውነት ፈላጊ ሆኗል። በመጽሐፍ ቅዱሱም ይሁን በቁርአን የሰው ልጅን ከተጠቀሰው ወንጌል አንቀጽ 5፥21 'ሁሉንም ፈትኑ መልካሙንም ያዙ' እንጂ በኑዛዜ ሃይማኖት ተቀብላችሁ ተቀመጡ ተብሎ አልተጻፈምና አውቆ ማንም ያስተምር ዘንድ መጽሐፏ ጥሩ ረድኤት ሆና ቀርባለች።

በዓለማችን ብዙ ሃይማኖቶች መኖራቸው ይታወቃል። ይሁን እንጂ ሁሉም ሰው ፈጣሪን ለመገዛት ይፈልጋል ማለት ያስቸግራል። ነገር ግን ፈጣሪ ማነው? እንዴትስ ይገኛል? ዛሬ አብዛኛዎቹ ሰዎች ትኩረት የሚሰጡት ለሃይማኖት መመሪያዎች ሳይሆን ለሃይማኖት አባቶች ነው። በዚህ ዙሪያ ከእስልምና እምነት ቁርአን፣ ከክርስትናም እምነት መጽሐፍ ቅዱስ ስለፈጣሪ ማንነትና ምንነት እንዲሁም <u>አመላለክ</u> የሚያስተምሩትን ነገር በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንመለከታለን። በዚህ ከተግባባን የሚከተለውን ያለ ጥላቻ በጥንቃቄ እያመዛዘን እንማማር።

# ምዕራፍ አንድ

## የፈጣሪ ሥልጣንና ደረጃው

ትንቢተ ኢሣይያስ ምዕራፍ 44፥24 እንዲህ ይነበባል፦ «ከማኅፀን የሠራሀ፥ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሁሉን የፈጠርሁ፥ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም ያፀናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ ከኔ ጋር ማን ነበረ?»

ወንጌላዊያን ግን ሰማይና ምድር ሲፈጥር አብሬ ነበርኩ ብሏል ኢየሱስ ይላሉ። የሚያቀርቡት ማስረጃ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1፥26 «ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር ይላል» እግዚአብሔር ያለው ኢየሱስን ነው አብረው ነው የፈጠሩት ይላሉ። ብቻዬን ነው የፈጠርኩት ያለው ነው የተሳሳተው? ወይስ አብሬ ነበርኩ ያለው? መልሱን ለአማኞች ትቻለሁ።

ትንቢተ ኢሳይያስ 46፥4-5 ደግሞ ይህንን በተመለከተ ተጫማሪ ሐሳብ አለው ይኸውም ዘፍጥረት 1፥26 ላይ ያለውን ሲቃወም እንዲህ ይላል «እስከ ሽምግልና ድረስ እኔ ነኝ፥ እስከ ሽበትም ድረስ እሸከማለሁ እኔ ሠርቻለሁ እኔም እነሣለሁ፤ እኔ እሸከማለሁ እኔም አድናለሁ። በማን ትመስሉኛላችሁ? ከማንስ ጋር ታስተካክሉኛላችሁ? እንመሳሰል ዘንድ ከማን ጋር ታስተያዩኛላችሁ?» ይላል።

ታድያ ሰው በማን ምስል ተፈጠረ? ለእግዚአብሔር ጥያቄ መልሱ ምን ይሆን? ሰውና አምላክ ይመሳሰላሉ ወይ? ከሆነ ምኑ ላይ? እንዴት? መልስ ያሻል።

ቁርአን ግን አላህ ሰው ይመስላል ከማለት የጠራ ነው። ለአላህ ተምሳሌት (አምሳያ) የለውም ነው የምለው።

ትንቢተ ኢሳይያስ 46፥9 «እኔ አምላክ ነኝና ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም።» ይላል። በተቃራኒ ደግሞ ሌላ ቦታ ላይ ቈላስይስ 1፥15 ኢየሱስን «የማይታየው የአምላክ ምሳሌ ነው» ይላል ማን ይሆን የተሳሳተው? ኢሳይያስ ወይስ ቈላስይስ? መልሱን ለአማኞች ትቻለሁ። ቁርአን ግን አላህ ሰውን ይመስላል ከማለት የጠራ ነውና እናስተውል።

ትንቢተ ኢሳይያስ 45፥11 «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ስለሚመጣው ነገር ጠይቁኝ፥ ስለ ልጆቼና ስለ እጄ ሥራም እዘዙኝ። እኔ ምድርን ሠርቻለሁ ሰውንም በእርስዋ ላይ ፈጥሬአለሁ እኔ በእጄ ሰማያትን ዘርግቼአለሁ።» ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። የሚገርመው ግን አምላክ የተባሉት ኢየሱስ ስለሚመጣው ነገር አላውቅም ማለታቸው

ነው እሳቸውን ውሸታም ለማድረግ። አምላክ ነህ ለሚሉት ግን መልሳቸው ምን ይሆን? አላህ ያውቃልና። ኢየሱስ አላወቁምና።

ማቴዎስ ወንጌል 24፥36 "ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም።" ይላል።

ኢየሱስ ናቸው የተሳሳቱት? ወይስ ኢሳይያስ? መልሱን አምላክ ነህ ላሉት ትቻለሁ። ቁርአን ግን ወደፊት የሚመጣውን ዐዋቂ አላህ ብቻ ነው ይላልና ከኢየሱስ መልስ ጋር አንድ ነው። ነቢይ ስለሆኑ ኢየሱስ (ዐ.ሰ) አይዋሹም። ሙስሊም ሁሉ ኢየሱስን /ዒሳን/ የመውደድ ግዴታ አለበት። የምንጠላቸው ከሆነ ተሳስተናል። ኦሪት ዘጸአት 33 ከ18-23 «እርሱም እባክህ ክብርህን አሳየኝ አለ፦ እግዚአብሔርም፦ እኔ መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ፣ የእግዚአብሔርን ስም በፊትህ አውጃለሁ፣ ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ፥ የምምረውንም እምራለሁ አለ። ደግሞም፦ ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ።»

ወንድሞቼ ደካማ ዓይናችን 60 ዋት አምፑል ማየት የማንችል ፍጡር ነን። ታውቃለህ አምላክህን ገርፈህ፣ ደብደብህ፣ መዶሻና ምስማር አዘጋጅተህ ልትሰቅለው ይቅርና ከእኛ የበለጠ ነቢይ ሙሴ በዓይኑ እንኳን ማየት እንዳልቻለ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ስለተናገረ ልባችንን ከፍተን ሳናመነታ ማመን አለብን እውነት ነውና።

ተጨማሪ የማቴዎስ ወንጌል 20፥20 ገነት ማስገባት አልችልም ይላል ኢየሱስሙሉ ቃሉ እንዲህ ይነበባል፦

«የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከልጆችዋ ጋር እየሰገደችና አንድ ነገር እየለመነች ወደ እርሱ ቀረበች። እርሱም ምን ትፈልጊያለሽ? አላት። እርስዋም እነዚህ ሁለቱ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ አንዱም በግራህ በመንግሥትህ እንዲቀመጡ እዘዝ አለችው። ኢየሱስ ግን መልሶ፦ የምትለምኑትን አታውቁም። እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? አለ። እንችላለን አሉት። እርሱም፦ ጽዋዬንስ ትጠጣላችሁ፣ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም አላቸው።»

ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል እንደተናገሩት ገነት ማስገባት የሳቸው ሥልጣን እንዳልሆነና ጠያቂዎቹ የሚለምኑትን አምላክ እንደማያወቁ በግልጽ አስተምረዋል። የእግዚአብሔርንም ሥልጣን ጉልህ አድርገዋል።

በዓለም ላይ ገነት ማስገባትን የሚያክል ሥልጣን ለማንም ፍጡር አልተሰጠም፣ ሊሰጥም አይችልም። በሰው እጅ ቢደረግ ኖሮ ግራ በተጋባ ነበር። እገሌ ይግባ? እገሌ አይግባ? ብሎ ለመወሰን በፍጡር

ዘንድ ፈጽሞ ስለማይቻል። ለዚህም ነው ኢየሱስ "እኔ የምስጥ አይደለሁም" ብለው ገለልተኛ የሆኑት።

የማቴዎስ ወንጌል 4፥9 «ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው። ያን ጊዜ ኢየሱስ፦ ሂድ አንተ ሰይጣን፤ ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው። ያን ጊዜ ዲያብሎስ ተወው።» ይላል።

ታዲያ ወንድሞቼ አምልኮትና ስግደት የሚገባው ለማን እንደሆነ ያወቀ ማን ይመስላችኋል? ለማንስ እንድንሰግድ ነው ኢየሱስ የመከሩን? ኢየሱስንስ ሲፈትነው የነበረ ሰይጣን አይደለምን? እግዚአብሔር ግን በክፉ ወይም በሰይጣን አይፈተንም እንጂ የለ? ኢየሱስ አምላክ ከሆኑ እንዴት በሰይጣን ተፈተኑ? የሚገርመው ግን የእግዚአብሔርን ስም ስንጠራ የሚሸሸው ሰይጣን አምላክ ናቸው የተባሉትን ኢየሱስን በቁጥጥሩ ሥር ካዋለ ታዲያ ኢየሱስ እንዴት ይመለካሉ? ሥልጣን ሙሉ በሙሉ ለ40 ቀን በሰይጣን እጅ ገብቶ ነበር ተብ ሏልና። እስቲ ይታያችሁ፤ ፈጣሪ በሰይጣን እጅ ለ40 ቀን እየተገመገመ ቆየ መባሉን ሕሊና እንዴት ይቀበላል?

አንድ ጊዜ ከአ/አበባ ወደ ድሬደዋ ስሄድ አውቶቡስ ውስጥ ይህ ጉዳይ ተነስቶ ኢየሱስ አምላክ ከሆነ እንዴት ተፈተነ? የሚለው በተሳፋሪዎች መካከል የውይይት ርዕስ ሆኖ ሁሉም በየተራ ሐሳቡን መስጠት ጀመረ። የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ አንድ አማኝ እንዲህ ነበር ያሉት ፦

"ኢየሱስ ለ40 ቀን መፈተኑ ሳይሆን ጌታ ያሰኘው ለ40 ቀን ያለ ምንም ምግብ መቀመጡ ነው። መቼም የሰው ልጅ ለ40 ቀን ያለ ምግብ መቀመጥ እንደማይችል ታውቃላችሁ።" ብሎ በመኪና ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለ10 ደቂቃ አፍ አስይዘው አሳምና ነበር። የሚገርመው ግን እራሳቸው ብዙም ሳይቆይ በበቂ ማስረጃ መያዛቸው ነው።

ጉዳዩ እንዲህ ነው፦ በመኪና ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ አዛውንት ወጣት ሴቶችና ወንዶች ባሉበት ከመሐል ፈርጠም ያለ ወጣት ተነስቶ ሁላችሁም በኢየሱስ ካላመናችሁ ገሃነም ትገባላችሁ፤ ኢየሱስ ሰው አይደለም ጌታ ነው፤ ሰው ቢሆን ኖሮ ለ40 ቀን ያለ ምግብ ባልተቀመጠ ነበር።" አለና ሰበካውን ፡በሰፊው አጧጧፈው። በልጁ ሁኔታ ያዙት ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በሰበካው አኩርፈው ማጉረምረም ጀመሩ። እኔም አላስችል ስላለኝ ሳላስብ የውይይቱ ተሳታፊ ሆንኩ።

በመጨረሻም ከብዙ ክርክር በኋላ ከዚህ የሚከተለው እሪት (ተውራት) እንቀጽ ተነበበ። "እሺ! ወገኔ ኢየሱስ ክርስቶስን 40 ቀን ያለ ምግብና ውሃ መኖሩ አምላክ ያሰኘዋል ብለሃልና እርግጠኛ ነህ? አልኩት" መልሱ "አዎ" የሚል ነበር ኮራ ባለ አንደበት። "ታዲያ

ኦሪት ዘጸአት 34፥7 ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር ለ40 ቀን ያለ ምግብና ያለ ውሃ በደረቅ ተራራ አሳልፈዋልና ሙሴን ማን እንበላቸው? አምላክ ከሆኑ የዙፋኑ ጌታ የቱ ይሆን? ሁለቱም ጌቶች ናቸው ወይ? 40 ቀን ያለ ምግብ መቀመጥ ጌታ የሚያደርግ ከሆነ ሙሴንስ ምን ልትል ይሆን? አምላክ ወይስ ሌላ? መልስ።" ስንለው መኪናው ውስጥ የነበረ ሕዝብ በጉጉት መልሱን ሲጠብቅ ዝምታ ብቻ ሆነ። መልስ በማጣቱ እኛም በእርሱ እያዘንን ድሬዳዋ ደረስን። እውነት አሸናፊ ናትና በአሁን ሰዓት ያ ሰባኪ እስልምናን ተቀብሎ ለአላህ ይሰግዳል። ጽናቱን ይስጠው። ወንድሞቼ ግራ አይግባን ኢየሱስ እራሳቸው ብዙ የሚሉት አላቸውና እስቲ እንከተላቸው። መካሪ ናቸውና እንስማቸው። መንገድ ናቸውና እንከተላቸው። ማቴዎስ 17፥20 ላይ እንደተናገሩት ወንድማችን ናቸውና እንውደዳቸው።

# ምዕራፍ ሁለት

## የፈጣሪ ሥልጣንና የኢየሱስ ክርስቶስ የሥልጣን ገደብ

ዮሐንስ ወንጌል 5:19 «ስለዚህ ኢየሱስም መለስ እንዲህም አላቸው፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ ሲያደርግ ያየውን እንጂ ወልድ (ኢየሱስ) ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም።» ይላል።

ፈጣሪ አምላክ ብቻውን ያደርግ የለም ወይ?

ኢሳይያስ 44:24 ተመልከት «ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ» ይላል። ይገርማል! ለብቻ ማድረግ ለአላህ አይሳነውምና በኩራት ይናገራል።

ማቴዎስ 24፥36 ላይ እንሂድ። ኢየሱስ ስለትንሣኤ ሲያስተምሩ፦ «ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም።» ማለትም የቂያማን ቀን ከአላህ በቀር ኢየሱስም አያውቁም። አላህ ግን ያውቃል ማለት ነው።

በተጨማሪ ትንቢተ ኢሳይያስ 44፥6 ላይ እንዲህ ይላል፦ «እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም። እንደኔ ያለ ማነው? ይነሳና ይጥራ፤ ይናገርም፤ ከጥንት የፈጠርሁትን ሕዝብ ያዘጋጅልኝ፤ የሚመጣውም ነገር ሳይደርስ ይንገሩኝ። አትፍሩ፣ አትደንግጡም፤ ከጥንቱ ጀምሬ አልነገርኋችሁምን? ወይስ አላሳየኋያችሁምን? እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ። ከእኔ ሌላ አምላክ አለን? አምባ የለም፤ ማንንም አላውቅም።» ይላል።

ታዲያ የሚመጣውን ሁሉ ዐዋቂ አላህ የትንሣኤን ቀን ያውቃል። ኢየሱስ እራሳቸው ከአብ በስተቀር ልጅም ቢሆን አያውቅም ብለዋል። እኔ አውቃለሁ አላሉምና እንማማር።

ምናልባት መልስ ካጠረን የኦሪት ሕግ ተሽሯል ትሉ ይሆናል። ነገር ግን ማን ሻረው? ኢየሱስ ከሆኑ ሕግን ከመሻር ነፃ ናቸው። እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፥» ብለዋል። (ማቴዎስ 5፥17 ይመልከቱ)። ሕግ አልተሻረም።

በዚህ ሐሳብ ላይ የዮሐንስ ወንጌል ጥሩ ማብራሪያ አለው። ኢየሱስና አብ የተለያዩ መሆናቸውንና አብ ከኢየሱስ እንደሚበልጥ እንዲህ ያስቀምጣል። ዮሐንስ ወንጌል 14፥28 «የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና» ይላሉ ኢየሱስ በአንደበታቸው። ይህን ካስተባበ ልን ኢየሱስን ብቻ ሳይሆን መጽሐፍአቸውንም ጭምር ማስተባበላችን ነውና እናስተውል።

ስለዚህ የግድ የአላህን በላጭነት ኢየሱስ መስክሯልና 'ላ ኢላሀ ኢልለሏህ' ማለት አለብን።

ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥5
«አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።» ይላል -ወንጌል። መካከል ብቻ ብሎ ቢተወው ባሻማ ነበር ነገር ግን ሰው የሆነ ክርስቶስ ብሎ አብራርቶታል።

ስለዚህ በእግዚአብሔር እና ሰው መካከል ያሉ ሰው የሆኑ ነቢይ ኢየሱስ መሆናቸውን ሳናመነታ መቀበል አለብን። ሰውማ ባይሆኑ ባልተራቡና ባልተጠሙም ነበር። ታዲያ ወንጌላዊያን ሰው ተብሎ የተመሰከረለትን ሰው አይደለም ነው የምንለው? ይህ ከሆነ መሳሳት አይሆንምን? እናስብ እንጂ ጉበዝ!

ወንድሞቼ ኢየሱስ የተወለዱት እንደ ማንኛውም ሰው በዘጠኝ ወር እንጂ አምላክ ይሆናሉ ተብሎ አንድ ወር እንኳን አልተመረቀላቸውም። ጡት እየጠቡ አደጉ እንጂ ግሉኮስ ከሰማይ አልተቀጠለላቸውም። ቢደረግም አያስደንቅም፡ አላህ ሥራው ብዙ ነውና!

መንፈስ ቅዱስ እንኳን የተሞሉት በዮርዳኖስ ወንዝ ካደጉ በኋላ ነው። ከዚያም በኋላ ሲጠሙና ሲራቡም ነበር። አላህ ግን ከመራብና ከመጠማት የጠራና እንዲያውም የተራበውንና የተጠማውን የሚያበላና የሚያጠጣ የተብቃቃ ጌታ ነው።

ኢየሱስ ስለመራባቸው ካልሰማችሁ ማርቆስ 11፥12 ኢየሱስ ተርቧል ብሎ አስቀምጦታል። የሚታይ ሐቅ ነውና እናንብብ።

አምላክ የሚራብ ከሆነ ታዲያ የተራበውን ማን ያብላ? ይታያችሁ አመዛዝና ማየቱን ለአንባቢያን ትቼአለሁ።

ሌላው ኢየሱስ የታቸው ወንድ ነው። ሉቃስ እንዳስቀመጠው መንፈስ ቅዱስ ወይም በሙስሊም አነጋገር ጂብሪል ወደ ማርያም በመጣ ጊዜ እንዲህ አላት፦ "ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ" ሉቃስ 1፥31 ይላል። አምላክን ግን በዚህ ዓለም ላይ ያየ የለም። ሙሴ እንኳ በመርፌ ቀዳዳ ያህል የፈጣሪን ብርሃን ባዩ ጊዜ ብርሃኑ ተራራ ላይ አርፎ ተራራው ቀለጠ። ሙሴም ወደቁ። ብርሃኑን እንኳ ማየት አልቻሉም። አምላክ ማለት የከበደ ነገር ነውና።

የማቴዎስ ወንጌል 27፥46 በዚህ ላይ ማብራሪያ አለው። ኢየሱስ እንደ ተባለው ከሁለት ወንበዴዎች መሃል ሆኖ ለስቅለት ሲዘጋጅ እንዲህ ብሏል ይላል ወንጌሉ፦ "ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ።" ይህ የሶሪያ ቃል "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ" የሚለውን ትርጉም ይሰጣል። ለመሆኑ ኢየሱስ ውስጣዊ ባሕሪው አምላክ ከሆነ ማንን ነው አምላኬ ያለው? ወይስ የሌለውን ነገር ያለ አስመስሉ ባዶ ሰማይ አምላኬ ብሉ ተጣራ? ወይስ አምላክ አለ? መልሱን ለአንባብያን ትቻለሁ።

የኔ አምላክ ግን ከመሰቀልና ከመዋረድ የጠራ ነው። ኢየሱስ ራሳቸው በኢስላም ዘንድ ትልቅ ክብር አላቸው። ተሰደቡ፣ ተገረፉ፣ ተገደሉ፣ ተሰቀሉ፣ ማለት ማቅለል እንጂ ማክበር አይደለም። ማለት ያለብን ግን በሰማይ በጀነት ውስጥ ተቀምጠዋል ነው። ለእርሳቸው ክብርም ይህ የተሻለ ነው እንጂ ከተቀበሩ በኋላ አመለጡ ማለቱ ክብራቸውን ይነካልና እናክብራቸው።

፩ ዮሐንስ ወንጌል 7፥28 ጥሩ ማብራሪያ አለው። እንዲህ ይላል፦ «እንግዲህ ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር፦ እኔንም ታውቁኛላችሁ፤ ከወዴትም እንደሆንሁ ታውቃላችሁ፤ እኔ በራሴ አልመጣሁም ነገር ግን እናንተ የማታውቁት የላከኝ እውነተኛ ነው።» አዎ የላከው እውነት ነው። የላከውን የሚያውቅና የሚያሳውቅ ሃይማኖት እስልምና ነው። ወገኖቼ ሳናመነታ አመዛዝነን እውነቱን እንቀበል።

ለመሆኑ ይህች አንቀጽ ብቻ ኢየሱስ ጌታ ነው ለሚሉት ሁሉ በቂ ማስረጃ አትሆንም ወይ?

በተጨማሪ ዮሐንስ ወንጌል 14፥24 «የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጅ የኔ አይደለም።» ይላል። ይህ እውነታ እያለ ግን መልዕክተኛ ነው ማለት ይከብደናል። ለምን? ኢየሱስ እራሳቸው አምላካቸውን ይለምናሉና እናንተስ ማንን ትለምናላችሁ? ማንንስ ታመልካላችሁ? ኢየሱስን ወይስ ፈጣሪ አምላካቸውን? ሙስሊም ግን የሚለምነው ፈጣሪን ብቻ ነውና አስብበትና ሳታመነቱ አመዛዝናችሁ እውነትን ተቀበሉ።

ዮሐንስ ወንጌል 14፥15 "እኔም አብን እለምናለሁ፣ ለዘላለምም ከናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል።» ይላል። ለማኝ ኢየሱስ ሲሆኑ ተለማኙ አላህ (ፈጣሪ) ነው።

እሺ ለማኝን ከመለመንና ተለማኙን አምላክ ከመለመን የቱ ይቀላል? ብዙውን ጊዜ ሲወራ ኢየሱስን አምላክ ካደረጉት ዋና ዋና መመዘኛዎች መካከል ከዚህ በታች የሚገኙት ተደጋግመው ከወንጌላዊያን ዘንድ ይነሳሉ፡-

(1) አልአዛርን ከሞት ስላስነሱ
(2) ያለ አባት ስለተወለዱ
(3) ወደ ሰማይ ስላረጉና ስላልተቀበሩ
(4) 40 ቀን ያለ ምግብ ስለቆዩ
(5) ተሰቅለው የሰዎችን ኃጢአት በሙሉ የተሸከሙ ስለ መሰላቸው
(6) ተዓምራትን በፍቃዳቸው የሠሩ ስለመሰላቸው

እነዚህ ዋና ዋና ሐሳቦች ሲሆኑ እንዲሁም የማስተማር ጥበብንና ተዓምራቶቹን እየጠቀሱ ጌትነታቸውን ሲያሳውቁና ሲያስተምሩ እንሰማለን። እስቲ እነዚህን ሐሳቦች አንድ ባንድ አንስተን እንመልከት፡-

## (1ኛ) አልአዛር የሚባለውን ሰው ኢየሱስ ከሞት ያስነሱት እንዴት ነበር?

ዮሐንስ ወንጌል 11፥41 ኢየሱስ ዓይኑን ወደ ሰማይ አንስቶ (ልመና/ዱዓእ) አደረገ። ሙሉ ቃሉ እንዲህ ይነበባል፡-

«አባት ሆይ! ስለሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ። ሁል ጊዜም እንድትሰማኝ አውቃሁ፤ ነገር ግን አንተ እንደላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለቆሙት ሕዝብ ተናገርኩ አለ።»

ይታያችሁ ኢየሱስ ጌታ ከሆነ የትኛውን ጌታ ለመነ? ወይስ የሌለውን ነገር ያለ አስመስሉ ተናገረ? ዓይኑንስ ወደ ማን አነሳ? ያመሰገነውስ ማንን ነው? መልሱ አምላኩን (አብን) ነው ካላችሁ ልክ ናችሁ። ከኛ በላይ ያለ እርሱ ብቻ ነውና። ታዲያ ይህ ኢየሱስን አምላክ ያደርጋዋልን? መልሱን ለአንባቢያን ትቻለሁ፣ ተወያዩበት።

## (2ኛ) ያለ አባት መፈጠሩ

ያለ አባት መፈጠር አምላክ የሚያደርገው ከሆነ አደም ያለ አባትና እናት መፈጠሩ ድርብ አምላክ ያሰኘው ነበር አይሆንም እንጂ። እናስተውል። ወደ እውነቱ እንመለስ።

ለምሳሌ በእጅ ባለ ብርጭቆ ውስጥ ውሃ መጨመር ይከብዳል? ወይስ በሌለ ብርጭቆ ውስጥ ውሃ መጨመር? የኢየሱስ አፈጣጠር ምሳሌው ይህ ነው ወገኖቼ። ማርያምን ከፈጠረ በኋላ በማኅፀኗ ኢየሱስን መፍጠሩ ይበልጥ ይደንቃል ወይስ ካለ እናትና አባት አዳምን መፍጠሩ?

## (3ኛ) ወደ ሰማይ ማረጉ

ኢየሱስ ሞተው ሳይቀበሩ ማረጋቸው አምላክ ካሰኛቸው ሌሎችም ያረጉ ሰዎች ስላሉ በአምላክ ዙፋን ላይ ያሉት እነማን ናቸው? ያረገ ሁሉ አምላክ ከሆነ ማለቴ ነው።

ኦሪት ዘፍጥረት 5፥24 ሄኖክ አርጓል። «ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና።» ይላል።

በተጨማሪ መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ምዕራፍ 2፥11-12 "ኤልያስም ወደ እግዚአብሔር በመንፈስ አርጓል።» ይላል። ታዲያ ማረጋቸው አምላክ ያደርጋቸዋልን? ከሆኑ ደግሞ ስንት አምላክ ሆኑ ማለት ነው?

እዚህ ላይ ሳልጠቅስ የማላልፈው ነገር አለ። ይኸውም ዮሐንስ ወንጌል 3፥13 ላይ ጥያቄ ስላለኝ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም ይላል። ከኢየሱስ በቀር ሌላ የለም ማለት ነው።

ታዲያ ሌሎችስ ወደ ሰማይ የወጡት ከሰማይ ነው የወረዱት ወይስ ኢየሱስ ብቻ? መልሱ ኢየሱስ ብቻ የሚል ከሆነ ቀጥሉ ያለውን የዚሁ ቀሪ ሐሳብ መቀበል አለብን ማለት ነው። ቀሪ ቃሉም «<u>እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው</u>» ይላል። ዮሐ 3፥13።

ይህ ቦታ የሚያስተምረን ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ ሰው ነበር ካረገ በኋላ አምላክ ሆኗል ለሚሉት ማስተባበያ ሲሆን ማስረጃ የሌለው ንግግር ለሚናገሩና የቃሉንም ትርጉም ለሚያጣምሙ ሁሉ ጥሩ ማስተማሪያ ነውና ልብ እንበል።

በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ፣ አምላክ ነው ብላችሁ አትሳሳቱ፣ ምክንያቱም ካረጉም በኋላ ኢየሱስ ሰው መሆናቸው ተጠቅሷልና። ሰው መሆናቸውን እንቀበል።

## (4ኛ) ያለምግብና ውሃ መቆየታቸው

ኢየሱስ 40 ቀን ያለ ምግብና ውሃ መቆየታቸው አምላክ ካሰኛቸው፣ በኦሪት ዘጸአት 34፥27 ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር ያለ ምግብና ውሃ ለ40 ቀን ተቀምጧልና ሙሴስ አምላክ ሊባል ነው ወይ? መልሱን ለአንባቢያን።

## (5ኛ) ኃጢያትን መሸከማቸው

እዚህ ላይ ሐቁ የአንድን ሰው ኃጢአት ሌላው የማይሸከም መሆኑ ነው። ቁርአንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያረጋግጡት ይህንኑ እውነታ ነው። ምን በወጣውና ምንስ ቸግሮት አንተ የሰበሰብከውን ወንጀልና ያጠራቀምከውን ኃጢአት ኢየሱስ ይሸከምልሃል?

አምላክ ደግሞ ኃጢአትን ይቅር እያለ የሚምር እንጂ እሱ የኃጢአት ተሸካሚ አይደለም። ኢየሱስ እራሳቸው ወደ ፈተና እንዳትገቡ በርትታችሁ ፀልዩ አሉ እንጂ ኃጢአታችሁን በሙሉ ተሰቅዬ ስለተለከብኩላችሁ የፈለጋችሁትን ሥሩ ብለው አላስተማሩም። ትጉና ፀልዩ ከኃጢአት ራቁ ነው ምክራቸው።

* ትንቢተ ሕዝቅኤል 18፥20-32 «ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች፣ ልጅ ያባቱን ኃጢአት አይሸከምም፣ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም፣ የጻድቁ ጽድቅ በራሱ ላይ ይሆናል፣ የኃጢአተኛውም ኃጢአት በራሱ ላይ ይሆናል። ኃጢአተኛ ካደረጋት ኃጢአት ሁሉ ቢመለስ ትእዛዜን ሁሉ ቢጠብቅ ፍርድንና ቅን ነገርንም ቢያደርግ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም። የበደለውም በደል ሁሉ አይታሰብበትም። በሠራው ጽድቅ በሕይወት ይኖራል። በውኑ ኃጢአተኛ ይሞት ዘንድ እፈቅዳለሁን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ከመንገዱስ ይመለስና በሕይወት ይኖር ዘንድ አይደለምን? ጻድቁ ግን ከጽድቁ ቢመለስ ኃጢአትንም ቢሠራ ኃጢአተኛውም እንደሚያደርገው ርኩሰት ሁሉ ቢያደርግ በሕይወት ይኖራልን? የሠራት ጽድቅ ሁሉ አትታሰብለትም፣ ባደረገው አመጽና በሠራት ኃጢአት በዚያች ይሞታታል።»

ታድያ ይህ እውነት የት ተጥሉ ነው? ኢየሱስ ከሆኑ ሕግን አልሻሩም። ይህን የእግዚአብሔር ንግግር ዘመን ሻረው ወይ? መልሱን ለኃጢአተኛ ሰው።

ታድያ ወንድሜ በሠራኸው ወንጀል ከተጠያቂነት አትድንምና በርታ ነው ምክሬ። ኃጢአት ከሠራህ ገሃነም፣ ጽድቅ ከሠራህ ጀነት የማይቀር ነውና አንታለል። አለበለዚያ እንኳን ሰውን ልናድን ምንም የማያውቀውን ሕዝባችንንም ኢየሱስ በማቴዎስ 23፥13 እናንተ ሰውን ከገነት ወደ እሳት ትከታላችሁ ያለው ቀጥታ ትርጉም የሚያገኘው በናንተ ላይ ነውና ፈጣሪን ፈርታችሁ እውነትን ተቀበሉ። ጥሪዬም ምክሬም ይኸው ነው። እንድትድኑ እንጂ እንድትጠፉ አይደለምና አስተውሉ።

ኢየሱስም ሆኑ ፈጣሪው የሚሉት በርትታችሁ ጸልዩ ነው እንጂ እናንተ እንደምትሉት በተሰፋ ቁጭ በሉ ደሙ ፈሷልና በደሙ ኃጢአታችን ተደምስሷል አይደለም። ታድያ ይህ ካልሆነ ከናንተና ከፈጣሪ ዐዋቂው ማነው? ከእናንተና ከኢየሱስስ ዐዋቂ ማነው? የፈጣሪውንና የኢየሱስን ቃል ትተን የማንን ቃል ይዘን ነው ተሸክሞላችኋል አትጨነቁ፤ የጌታ ልጆች ችግርም የለብንም የምንለው? ሁሉንም ፈትኑ መልካሙንም ያዙ ይላልና አስቡበት።

(6ኛ) ተዓምራትን በመሥራታቸው

ኢየሱስ ብቻ ናቸው ወይ ተአምራትን የሠሩ? ለመሆኑ ሙሴ በአንዲት በትር ስንት ተአምራትን ሠራ? በእጁስ ምን ሠራ? እስቲ እንመልከት። በመጀመሪያ ሙሴ በትሯን እባብ አደረጋት። ከዚያም መልሶ በትር አደረጋት። ባሕርን የሚያህል ነገርም ለሁለት ሰነጠቀባት። ከዚያም የፈርዖንን ጭፍራ በሙሉ ደመሰሰባት። ምድረ እስራኤልን ሙሴ ነገሰባት። ይህን ሁሉ ተዓምር በእግዚአብሔር ፈቃድ የሠራው በአንዲት ዱላ ነው። ከዚህም አልፎ ሙሴ እጁን እንደ ብርሃን እያበራ ይጠቀምበት ነበር። የሚታወቅ ሐቅ ነው ተአምር አይደለም ወይ? ተአምር ሠሪ ኢየሱስ ብቻ አይደሉምና አንታለል። የታምራትና የፈውስ ነገር ከተነሳ ብዙ ብዙ ማለት ይቻላል። እያንዳንዳቸው ነቢያት የራሳቸው የሆነ ተአምራት ተሰተጧቸተዋል።

ለምሳሌ ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ አንድ ኩባያ ወተትን ከሰባ ሰዎች በላይ ጠግበው እንዲጠጡና እንዲተርፍ አድርገዋል። ለምሳሌ ያህል አነሳን እንጂ ብዙ ብዙ ማለት ይቻላል።

የሚገርመው ታድያ ይህ ሁሉ ታምራት ሲደረግ አንድም ነቢይ በችሎታዬ አደረግሁ አላለም። ነቢያት ሁሉ ይህን በማድረጋቸው አምላክ ተደርገው አልተመለኩም። በአምላክ ፍቃድ እንጂ በችሎታቸው አልሠሩምና።

ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 5፥19 ላይ እንዳለው ሁሉ፦
«አብ ሲያደርግ ያየውን እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም» ነው ነገሩ።

የንግግር መብዛት ትርጉም የለውም። እውነት ካለበት ትንሽ ምሳሌ ይበቃል። እንኳን ነቢይ ተራው የሰው ልጅ ብዙ ተዓምራትን እየሠራ ነውና አንታለል።

ስለዚህ እላይ ለፈለገው ተዓምር ማድረግን መስጠቱ ሥልጣኑን አያስነጥቀውምና ጠንቀቅ እንበል።

## ምዕራፍ ሦስት

## ኢየሱስ ከአላህ ተልከው መጡ ወይስ በራሳቸው ፍላጎትና ችሎታ?

እንደሚታወቀው ነቢያት ከፈጣሪ አምላክ ወደ ሰው ልጆች ይላካሉና ኢየሱስም በዚህ ላይ ብዙ ቦታ በማያሻማ መልኩ መላካቸውን ገልጸዋል። አምላክ እንጅ መልዕክተኛ አይደሉም የምትሉ ይህን አንብቡ፦

ዮሐንስ ወንጌል 12፥44-50 «በኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ እንጂ በኔ አይደለም።» ይላል።

ዮሐንስ 14፥24 «የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጅ የኔ አይደለም።» ይላሉ ኢየሱስ በአንደበታቸው።

ዮሐንስ ወንጌል 11፥42 «አባት ሆይ ስለሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ ሁል ጊዜም እንድትሰማኝ አውቅሁ፤ ነገር ግን አንተ እንደ ላከኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለቆሙት ሕዝብ ተናገርኩ አለ።» ኢየሱስ።

ዮሐንስ ወንጌል 8፥29 «የላከኝም ከኔ ጋር ነው፤ እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና አብ ብቻዬን አይተወኝም አላቸው።» ኢየሱስ እራሳቸው።

ዮሐንስ ወንጌል 8፥40 «ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኳችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ» አላቸው። ሰምቶ ማስተላለፉ አምላክ ያደርገዋል ወይ?

ዮሐንስ ወንጌል 8፥54 «ኢየሱስም መለሰ አለም፡- እኔ ራሴን ባከብር ክብሬ ከንቱ ነው፤ የሚያከብረኝ እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው። አላወቃችሁትምም፤ እኔ ግን አውቀዋለሁ። አላውቀውም ብል እንደናንተ ሐሰተኛ በሆንሁ፤ ዳሩ ግን አውቀዋለሁ ቃሉንም እጠብቃለሁ።» ታዲያ መቼም ኢየሱስ የአላህ መልዕክተኛ ስለ መሆናቸው ራሳቸው በቂ ማብራሪያ ሰጥተዋልና እንታዘዝ። ሐሰተኛ ከመሆን ተጠንቀቁ ከማጋራት ራቁ። ይህ ነው ሐቁ።

በተለይ «እናንተ አታውቁም እኔ ግን አውቀዋለሁ አላውቀውም ብል እንደ እናንተ ሐሰተኛ በሆንሁ» ብለው የተናገሩት ሁለት ፍሬ ሐሳብ በውስጡ አቅፏል።

- እነሱ አላህን ከጂና ሐሰተኛ መሆናቸውን
- እሳቸው ግን አላህን የሚያውቁና ያልካዱ መሆናቸውን።

ነገር ግን በፍጹም አልተላኩም ኢየሱስ ራሳቸው ላኪ አምላክ ናቸው የሚሉት ወንጌላዊያን ኢየሱስን ማስዋሸታቸውን አልተረዱም ይሆን?

ውሸት በመናገራቸው ማፈራቸው በአላህ እምላለሁ የማይቀር ሐቅ ነውና ያስተዛዝባልና ይቅር እላለሁ።

አንባቢያን ሆይ! እስልምና መጥፎ ሃይማኖት ነው ኢየሱስን ተተን ከኋላ የመጣውን ሙሐመድን እንዴት እንቀበላለን? ትሉም ይሆናል። ነገር ግን ነቢያችን የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ ነቢይ ናቸው እንጂ በትንሣኤ (በቂያማ ቀን) ከፊት (የመጀመሪያ) መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል።

«ኋለኞች ፊተኞች ይሆናሉ፣ ፊተኞች ኋለኞች ይሆናሉ።» ይላል የማይሻር ቃሉ። (አልሐምዱ ሊላህ) በትንሣኤ ቀን ፊተኛ መሆናችንን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መኖሩን በማየትና በመስማት ብዙ ሰዎች በአሁኑ ሰዓት በጥርጣሬ ውስጥ ይገኛሉ። አሰሟቸው ያስቡበትና በጥርጣሬ ይውጡ። የሰው ልጅ ወደ እውነተኛ ብርሃን መውጣትን እየፈለገ ነውና።

# ምዕራፍ አራት

## ኢየሱስ ብቻ የእግዚአብሔር ልጅ ተባሉ ወይስ እኛም?

ብዙን ጊዜ ኢየሱስ አምላክ አለመሆናቸውን ለክርስቲያኖች በቂ በሆነ ማስረጃ ገልጠህ ካቀረብክላቸውና ሲረዱ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ወደሚለው ዝቅ ይላሉ። ከአምላክነት ወደ ልጅነት ዝቅ ያደርጓቸዋል። ለዚህም ቢሆን መጽሐፉ ጥሩ መልስ በመስጠት ሐሳባቸውን ይቃረናል።

ማቴዎስ ወንጌል 23፥8 «እናንተ ግን መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ስለሆነ (ኢየሱስ ማለት ነው።) እናንተ ሁላችሁም ወንድማማች ናችሁ። አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና።»

አዎ የሰማዩ አባታችን ነው ምክንያም አባታችን አደምን የፈጠረው እርሱ ነውና። አላህ ሚስት አግብቶ ሳይሆን ያለ ምንም አባትና እናት በራሱ እጅ ሥራ ሰው ካደረገው በኋላ ሕይወት ዘራበት። አደም ብሎም ሰየመው። አላህ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ነው። የሰውም የእንስሳትም ፈጣሪና አባት ነው።

አላህ አደምን መንፈስ ቅዱስ ልኮ ሳይሆን ስሙን ሰይሞ የጠራው በቀጥታ ራሱ ነው። ኢየሱስ ግን ጂብሪል ተልኮ ስሙ ተሰይሞ ለመርየም ኢየሱስ በዱው ተብላ ነው የተሰየመው። አላህ ልጅ ቢኖረው ኖሮ የመጀመሪያ ልጁ አደም በሆነ ነበር። ይህን ታላቅ የኢየሱስን ንግግር ማለትም <u>የሰማይ አባታችሁ</u> ብሉ የተናገረውን በመተው ልጅነቱን ለኢየሱስ ብቻ የምንሰጠው ለምን ይሆን? አላህ በፈለገው ዓይነት ፍጡራንን ይፈጥራልና የሚሳነው ነገር የለም። አባካችሁ አንታለል።

ካለአባት ከእናት ብቻ የተፈጠረ ኢየሱስ ነው። አይደለምን? ካለ እናትና ካለ አባት የተፈጠረ አደም ነው። ከአደም ጎን የተፈጠረች ሄዋን ነች። ከዚህ ከሦስቱ አፈጣጠር የቱ ነው የሚደንቀው? የትኛው ነው የእግዚአብሔር ልጅ የሚመስለው? ካለ አባትና እናት የተፈጠረ አደም ወይስ ካለ አባት ነገር ግን ከእናት ማኅፀን የተፈጠረ ኢየሱስ? አገናዝቡ እስቲ። ይህን ስል አደም ልጅ ነው ማለቴም አይደለም። አላህ አይወልድምና።

ማቴዎስ ወንጌል 6፥1 «ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተንጠቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት <u>ባለው</u> <u>አባታችሁ</u> <u>ዘንድ</u> ዋጋ የላችሁም።» ይላሉ ኢየሱስ። አዎ በሰማይ ባለው አላህ

ዘንድ ዋጋ ያጣ ሰው እውነትም ዋጋ የለውም። እርሱ ያልተከለው ሁሉ ይነቀላልና።

የማቴዎስ ወንጌል 6፥32 ተጨማሪ ሐሳብ አለ «ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ <u>አባታችሁ</u> ያውቃልና።» ይላሉ ኢየሱስ።

ስለዚህ በሰማይ ያለው አባህ ለሁላችንም ጌታና አባት ነው እንጂ ለነቢያችን ለኢየሱስ ብቻ አይደለም። ሁላችንም የተጠቀሰውን ቃል በመደገፍ ወደ ገደል እየገባ ያለውን ሕዝብ በኅብረት እናድን እላለሁ።

ከላይ የተዘረዘሩትን እውነት ያስቀመጡልን ጸሐፊዎች ከራሳቸው ፈጠራ ነው ማለትም አንችልም። መቀነስ፣ መጨመር፣ ለመቅስፍት ያደርሳልና እርሳቸውንም በማስዋሸት ያልተናገሩትን ትርጉም አንጠቀም። በእርጋታ ተመልከቱ እላለሁ።

ከምላስ ማብራሪያ ይልቅ የተጻፈውን ወንጌል ይበልጥ በመረዳት ከማስረጃ ጋር በማገናዘብ እንረዳዳ፣ እንማማር።

# ምዕራፍ አምስት

## ጳውሎስ ማነው?

የጳውሎስ ነገር ከተነሳ ብዙ አጠያያቂ ጉዳዮች አብረው ይነሳሉ። እርሱ ግን ሐዋርያ መባል ቀርቶ ኢየሱስን አንድም ቀን በዓይኑ አላየም። ቢያገኘው እንኳን ጳውሎስ ኃይለኛ አሳዳጅ ስለነበር ኢየሱስን ከመግደል ወደኋላ አይልም ነበር።

ይህ በመላው ክርስቲያን ዘንድ ድሮ በአሳዳጅነቱ የሚታወቀው ጳውሎስ ኢየሱስ ካረገ በኋላ መንፈሳዊ ሆኛለሁ፣ በራዕይ (በሕልም) ኢየሱስን አይቸዋለሁ፤ ኢየሱስ አምላክ ነው ብላችሁ ተቀበሉ፤ በማለት ኢየሱስም ሐዋርያትም ያልተናገሩትን የኢየሱስን አምላክነት በሰፊው ያወጀ ሰው መሆኑ ግልጽ ነው። ስመቀጠልም የግል መልእክቱን 14 ጊዜ ለ11 ሀገሮች ማለትም ከሮሜ ሰዎች እስከ ዕብራውያን ድረስ አሰራጨ። ጳውሎስ ያስበተነው መልዕክት እንደ አምላክ ቃል ተቆጥሮ መወሰዱ ከማስገረም አልፎ የእውቀት ባለቤቶችን ጉድ ማሰኘቱ አልቀረም።

ምክንያቱም ብዙ ዘመን ከኢየሱስ ጋር አብረው በልተው ጠጥተው መከራን አይተው ትምህርቱንና ገለጻውን በዓይናቸው ካዩ ሐዋርያት ንግግር ይልቅ የጳውሎስ ሕልምና ራዕይ ታላቅ ሥፍራ ይዞ ተቀምጧልና።

ስለመሆኑ ለ12ቱ ሐዋርያት የሐዋርያነት ሥልጣን ማን ሰጣቸው? የሚለውንና ስለ ጳውሎስ እስኪ እንመልከት።

የሐዋርያት ሥራ 26፥13 «ብመንገድ ሳለሁ እኩል ቀን ሲሆን በዙሪያዬ እና ከእኔ ጋር በሔዱት ዙሪያ ከፀሐይ ብሩህነት የበለጠ ብርሃን ከሰማይ ሲበራ አየሁ። ሁላችንም በምድር ላይ በወደቅን ጊዜ፦ ሳውል ሳውል፥ ስለምን ታሳድደኛለህ? የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል የሚል ድምጽ በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲናገረኝ ሰማሁ። እኔም፦ ጌታ ሆይ፥ ማን ነህ? አልሁ። እርሱም አለኝ፦ አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ።"

በዚህ ዓይነት ነበር ጳውሎስ ኢየሱስን አየሁ ያለው። "ለምን ታሳድደኛለህ?" ብሎ ሲጠይቀው "ጌታ ሆይ! ማንህ?" አለው። ጳውሎስ ገና ኢየሱስ ማንነቱን ሳይነገረው የጌትነትን ሥልጣን አሸከመው። ጳውሎስ ከዚያም በኋላ ነው "የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ" የሚል መልስ ያገኘው። ጳውሎስ ያናገረውን ሰው ማንነት ሳያውቅ ጌታ ማለቱን ማን አስተማረው? ኢየሱስም ቢሆን እኔ ጌታ ነኝ መች አለ?

ከቃሉ እንደምንረዳው ኢየሱስ እንኳን ቢሆን ኢየሱስ ነኝ አለ እንጂ አምላክ ነኝ የሚል ንግግር አልወጣውም ማለት ነው። ታድያ የእግዚአብሔር ቃል መንፈስ ሁሉ እውነት አይደለምና መርምሩ ይላል። የጳውሎስን መንፈስ ለመሆኑ ማን መረመረ?

ዘካሪያስ 10፥2 «ሕልምንም የሚያዩ በሐሰት ተናግረዋል፥ በከንቱም ያጽናናሉ!» ይላል።

ሉቃስ 9፥1 ላይ ለሐዋርያት ሥልጣን የሰጣቸው ኢየሱስ ነው። ለጳውሎስ ግን ሥልጣን የሰጠው ጳውሎስ እራሱ ወይም ሕልሙ መሰለኝ። ምክንያቱን እንመልከት።

1ኛጢሞቴዎስ 2፥7 «እኔም ለዚህ ነገር አዋጅ ነጋሪና ሐዋርያ በእምነትና በእውነትም የአሕዛብ አስተማሪ ለመሆን ተሾምሁ፤ እውነት እናገራለሁ፤ አልዋሽም» ይላል ጳውሎስ። ሌላው የሐዋርያት ሥራ 26፥24 ጳውሎስ «እንዲህም ብሎ ስለራሱ ሲመልስ ፊስጦስ በታላቅ ድምጽ፦ ጳውሎስ ሆይ፥ አብደሃል እኮ፤ ብዙ ትምህርትህ ወደ እብደት ያዞርሃል አለው።»

ታድያ! አንባቢያን አጠገቡ የነበሩና ያሉ ሰዎች እንኳን ስለሱ መታወክ በትክክል አስቀምጠዋልና ብዙ የምለው ነገር የለኝም። በወቅቱ አብሮት ከነበረ ሰው የበለጠ ስለ ጳውሎስ የሚያውቅ ዛሬ ያለ አይመስለኝም። ሊኖርም አይችልም። በይበልጥ ለመረዳት ካስፈለጋችሁ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ጳውሎስ ያፈርሰዋልና እንዴት አድርጎ እንደሚያፈርሰ እንመልከት። ሁሉንም ፈትኑ መልካሙንም ያዙ።

ማርቆስ 12፡29 ላይ ስለ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ኢየሱስ ሲጠየቁ፦ «ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ፦ እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን

አንድ ጌታ ነው፥ አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት።» ብሉ መልሰዋል።

ጳውሎስ ግን ተቃራኒ ሐሳብ አለው። ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6፥3 ላይ የፊተኛይቱን ትእዛዝ እንዲህ አስቀምጧታል።
«አባትህና እናትህን አክብር፤ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት።» ይላል ፊተኛይቱ ትእዛዝ በእስልምና ሃይማኖት ላ ኢላሀ ኢልለላህ ማለትም አንድ አላህ እንጂ ሌላ ሐቀኛ አምላክ የለም የሚል ሲሆን ይኸውም ኢየሱስ ከተናገሩት ቃል ጋር አንድ መሆኑን በትክክል ያስረዳናል።

ይህ ከኢየሱስ የተለየ አውቃለሁ የሚለው ጳውሎስ በእርግጥ ተሳስቷል። እሱ እራሱ ስለራሱ ማንነት ገልጧልና እናስተውል። ከባለቤቱ በላይ ያወቀ ቡዳ ነው ይባል የለ?

ጳውሎስ ስለራሱ እንዲህ ይላል፡- ወደ ገላቲያ ሰዎች 1፥13 «ብአይሁድ ሥርዓት በፊት እንዴት እንደኖርሁ ሰምታችኋልና የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ያለ ልክ አሳድድና አጠፋ ነበር፥» ይላል።

1ኛ ቆሮንቶስ 15፥9 «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ» ይላል።

በድፍረት እራሱን ከአምላክ ፀጋ ያደርጋል። ስለራሱ ጽድቅም ይመሰክራል። ነገር ግን ኢየሱስ ራሱ እኔ ስለራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም ይላል።

በዮሐንስ ወንጌል 5፥31 ኢየሱስ ስለራሴ ብመሰክር ምስክርነቴ ብቁ አይደለም እያለ ጳውሎስ ግን እሱ ብቻ ስለ ራሱ መስክሮ እውነት ተብሎ መታመኑ በጣም አስገርሞኛል።

ኢየሱስ የሚፈወሱትና የነቢይነት ሥልጣናቸው ለሕዝበ እስራኤል ብቻ መሆኑን በማቴዎስ ወንጌል 15፥24 ላይ በማያሻማ መልኩ-
«ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላኩም» ብለዋል። ጳውሎስ ግን፦ 1ኛ ዮሐንስ መልክት ምዕራፍ 2፡2 «እርሱም (ኢየሱስ) የኃጢአ ታችን ማስተስሪያ ነው፥ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ» ይላል ጳውሎስ።

ኢየሱስ ግን ሕግንና ነቢያትን ልሽር አልመጣሁም እንዳሉ ሰምታችኋል አንብባችኋል። ታዲያ ይህን ሰው ማን እንበለው? መልሱን ለናንተ።

የጳውሎስ ንግግሮች ከማስገረማቸውም በላይ እርስ በርሳቸውም ይቃረናሉ። አንዳንድ ቦታ ላይ ኢየሱስን ጌታና አምላክ ሲያደርግ ሌላ ቦታ ደግሞ ኢየሱስ ራሳቸው አምላክ እንዳላቸው ይናገራል። ለምሳሌ፦

2ኛ ቆሮንቶስ 1፥3 «የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ» ይላል። አዎ ኢየሱስ አምላክ አላቸው ዓለማችንም ያላት አምላክም አንድ ነው። ከሱም ሌላ የለም። ክብርና ስግደትም ይገባዋል።

1ኛ ቆሮንቶስ 8፥4 «አንድ አምላክ አብ ነው» ብሎም ጳውሎስ አስተምሯል። እንመልከት ሙሉ ቃሉ እንዲህ ይነበባል፦ «እንግዲህ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ስለመብላት፥ ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደሆነ ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን። መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድርም ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ፥ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ፥ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በርሱ በኩል የሆነ።» ይላል ጳውሎስ።

ታዲያ አንባቢያን ሆይ! አብ አምላክ ከሆነ ከወልድ አልተለየም ወይ? ሥላሴዎችን የሚያገናኛቸው መጽሐፍ ቅዱስ የትኛው ይሆን?

የትኛው መጽሐፍ ይሆን ለሁለቱም የጋራ አምላክነት እንዲጋሩ የሰጣቸው? ሦስተኛው አምላክስ መንፈስ ቅዱስስ የት ገባ? በጳውሎስ ትምህርት አብ ብቻ አምላክ ተብሏልና። መልሱን ሥላሴዎችን ለሚያመልኩ ትተናል።

ዮሐንስ 14፥28 ላይ ኢየሱስ «ከእኔ አብ ይበልጣና» ያሉትን አይበልጥሀም ትዋሻለህ እንበለው ወይ? ኢየሱስ ግን ከውሸት የጠሩ ነቢይ ስለ መሆናቸው በማርቆስ 6፥3-4 ከመጠቀሱም በላይ በቁርአን ምዕራፍ 5፥75 ልብን በሚያረጋጋ መልኩ ተቀምጧልና ቁርአንን ያንብቡ እላለሁ።

# ምዕራፍ ስድስት

## ኢየሱስ ስለፈጣሪያቸው የተናገሩት ቃል

ዮሐንስ ወንጌል 14፥1 «ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ» ብለዋል ኢየሱስ።

ኢየሱስ አምላክ ከሆኑ ለምን በራሴ ቤት አላሉም?

ዮሐንስ ወንጌል 12፡49 «እኔ ከራሴ አልተናገርሁምና ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ» ይላል።

ትእዛዝ የሰጠኝ አብ ነው እያለ አምላክ ይሆናል? ከሆነስ አምላክን ማን አዘዘው? የታዘዘውስ ማነው? ለመሆኑ አምላክን የሚያዝ አምላክ አለ? የለም ሊኖርም አይችልም።

ማርቆስ 10፥17 «እርሱም በመንገድ ሲወጣ አንድ ሰው ወደ እርሱ ሮጦ ተንበረከከለትና፦ ቸር መምህር ሆይ፥ የዘላለም ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም፦ ስለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም» ይላል።

አላህ ቸር ሲሆን ኢየሱስ ግን አይደለሁም ብለዋል። ኢየሱስ አምላክና ቸር ከሆኑ ቸርነቱን ለምን ተቃወሙ?

<u>ለኢየሱስ ሕይወትን በቸርነቱ የሰጠው ማነው</u>? የኢየሱስና የፈጣሪያቸው ሕይወት አንድ ናት ወይ? አንዳንድ ጊዜ በአካል ሦስት ናቸው፥ በሕይወት (በመንፈስ) አንድ ናቸው ሲባል ግራ ይገባችሁ ይሆናል። መልሱን መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል 5፥26 አብና ወልድ የተለያዩ መሆናቸውን ይገልፃል። ኢየሱስ ሰው መሆኑንም ይናገራልና እንከታተል።

ሙሉ ቃሉ «አብ በራሱ <u>ሕይወት</u> እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ <u>በራሱ ሕይወት</u> እንዲኖረው ሰጥቶታልና። <u>የሰው ልጅም</u> ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው» ይላል።

ሥልጣን ለነቢያት (ለወልድ) ሰጪ ማነው? አላህ (አብ) ማለት አይደለምን? የተሰጠውም ሥልጣን በምድር ላይ ማለት ነው። ኢየሱስ በትንሣኤ ቀን ግን የምፈርድባችሁ እኔ አይደለሁም ብሏልና። ሁለት ባለሥልጣን (ሁለት አምላክ) የለም። ሕይወት ሰጪ አምላክ አንድ አላህ ብቻ ነውና የሚከተለውን ጥያቄ እንመልከት፦

<u>ጥ.1</u> ለወልድ ሕይወት የሰጠው አብ ከሆነ ለአብስ ማን ሕይወት ሰጠው?

<u>ጥ.2</u> ኢየሱስ ሰው ከሆኑ ጌታስ ማነው? ሰው ጌታ ይሆናል ወይ?

በምድር እያለ ሰው ነው ካረገ በኋላ አምላክ ነው ትሉ ይሆናል። ለዚህ ግን ዮሐንስ ወንጌል 3፥13 ጥሩ መልስ አለው፦

«ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው።» ከምድር ወደ ሰማይ የወጣው እራሱ ኢየሱስ ሰው ማለት ነውና እንረዳ።

ማርቆስ 14፥42 የሰው ልጅ በኃይል በስተቀኝ ይቀመጣል ይላል። ካረገ በኋላ አምላክ ነው የምትሉ ሁሉ ስህተታችሁን ከዚህ ተማሩ እንላለን።

በሌላ በኩል ኢየሱስን ያላመለከ ሕይወት የለውም (ጀነት አይገባም) ኢየሱስን ጌታ ነው ያላለ አብን (አላህን) ብቻ ቢለምን ዋጋ የለውም ትሉ ይሆናል። ኢየሱስ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ያሉት ነገር አለና እንከታተል።

ማቴዎስ 15፥13ትን ይመልከቱ። «የሰማዩ አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል» ይላል። በተጨማሪ ማቴዎስ 7፥21 «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት (ጀነት) የሚገባ አይደለም። በዚያን ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? የዚያን ጊዜም፦ ከቶ አላወቃችሁም እናንተ አመጸኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባችኋለሁ» ይላል ።

ኢየሱስን ጌታ ማለት ፈጽሞ ጀነት አያስገባም። የአላህን ፈቃድ ማሟላት እንጂ። ሟትና ማታ በስህተት የተጨነቁበትን የኢየሱስን ጌትነትና አምላክነት ለማስተማር መድከሙ ኢየሱስ ያልፈለጉትና ያልደከመበት ርዕስ ነው። ፍላጎቱ ለክብሩ እንዲለፉ አለመሆኑና በኢየሱስ ስም ሰይጣን ማውጣቱ ጀነት (the kingdom of the heavens) የሚያስገባ አይደለምና እንታለል። ምክንያቱም ጌታ ያሉት እንኳ በማቴዎስ 7፥21 ላይ ሐሰተኞች ተብለዋል። ኢየሱስን ብቻ ጌታ ማለታቸው ሐሰተኛ ያስብላቸዋልና እንታለል። የአብን ጌትነት እናውጅ እላለሁ።

ማቴዎስ ወንጌል 15፥9 በከንቱ ያመልኩኛል ይላል ኢየሱስ ሙሉ ቃሉ ይቀጥላል፦

«የሰውም ሥርዓት የሆነን ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል»። ኢየሱስ ያልፈለገውን ነገር በግድ ሲያመልኩት ስለጠላና እንዲያመልኩት ስላልፈለገ ከንቱነታቸውን አስተማረ ማለት ነው።

ፈጣሪ አምላክ (አላህ) ግን አምልኩኝ፣ ተገዙኝ፣ አምላካችሁ ነኝና ስገዱልኝ፣ ቸር አምላክ ነኝና ለምኑኝ፣ ከፍ ከፍ አድርጋችሁ እዩኝ፣ ከኔ የበለጠ የለምና ተገዙኝ ይላል እንጂ አታምልኩኝ አይልም። ማንን ፈርቶ? ለማንስ ሥልጣኑን ትቶ? ቸር አይደለሁም ላገለግል ነውና የመጣሁት አታምልኩኝ፣ ግረፉኝ፣ ስቀሉኝ፣ ትፉብኝ የሚለው አምላክ ምን ቢቸግረው ይሆን?

አላህ (አምላካችን) አምልኩኝ፣ ተገዙኝ፣ አለዚያ ግን እቀጣችኋለሁ፣ ከልካይ የለብኝም የሚል ጌታ ነው እንጂ ሰው መስሎ ሞቶ የሚነሳ አምላክ አይደለም።

# ምዕራፍ ሰባት

## ያለፉት ነቢያትና የሙስሊም ጸሎት ሲነጻጸር

**ትጥበት (ውዱእ)**

ለምን ትታጠባላችሁ? በጀናባና ያለ ውዱእ ብትሰግዱስ አምላክ አይሰማም ወይ? በቀን አምስቴ መታጠቡ ለምን አስፈለገ ተብላችሁ ይሆን? መልሱን ከመጽሐፍ ቅዱስ ያገኛሉ ይከታተሉን።

ኦሪት ዘጸአት 40፥30 «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው የመታጠቢያውን ሰን በመገናኛው ድንኳንና በመሰዊያው መካከል አኖረ፥ ለመታጠቢያም ውሃን ጨመረበት በእርሱም ሙሴና አሮን ልጆቹም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ታጠቡ፤ ወደ መገናኛው ድንኳን በገቡ ጊዜ ወደ መሰዊያውም በቀረቡ ጊዜ ይታጠቡ ነበር።» ሙስሊሙንም ለትጥበት ያዘዘው ያው የሙሴ አምላክ ነው። በነቢዩ ሙሐመድ ﷺ አልተጀመረም ።

ሐዋርያ 7፥33 «ጌታም የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች ምድር ናትና የእግርህን ጫማ አውልቅ።» ጫማ አውልቆ መስገድ በነቢዩ ሙሐመድ ﷺ አልተጀመረም። ታጥበን እንስገድ መባሉ በሙስሊም አልተጀመረምና ከሙሴ እንማር። የተቀደሰ ስፍራ ሁሉ በጫማና በቆሻሻ ነገር እንደማይረገጥ መማር መቻል አለብን።

**የጀናባ (በግብረ ሥጋ ግንኙነት የረከሰ ሰው) ትጥበት**

ማጋነን አይሁንብኝና ከኢስላም በስተቀር ለጀናባ ትጥበት የሚጨነቅ አማኝ አላጋጠመኝም። መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይል ይሆን? መልሱን ከመጽሐፍ ቅዱስ ያገኙታል።

ኦሪት ዘዳግም 23:10 «በእናንተ መካከል ሌሊት በሚሆነው ርክሰት የረከሰ ሰው ቢኖር፥ ከሰፈር ወደ ውጭ ይውጣ፣ ወደ ሰፈርም አይግባ፤ በመሸም ጊዜ በውሃ ይታጠብ፣ ፀሐይም በገባ ጊዜ ወደ ሰፈር ይመለስ።»

በተጨማሪ በኦሪት ዘሌዋውያን 15፥18 «ወንዱ በሴቲቱ ቢደርስባት ሁለቱም በውሃ ይታጠቡ፤ እስከ ማታም ድረስ ርኩሶች ናቸው።» (ኦርኩስ ማለት ነጂስ ማለት ነው።)

ታዲያ ይህ እውነት የት ተደበቀና ነው በጀናባ የምንኖረው? ሕዝብ ፊት ለፀሎት በጀናባ (በርክሰት) የምንቆመው? ኢየሱስ ሕግን አልሻርኩም ብለዋል። ይህ የጀናባ ጉዳይ ከቁርአን በተለየ መልኩ ታጥቦ እንኳን ወደ ሰፈር ካልመሸ አይግባ ተብሉ የተጻፈውን እውነት

እንዴት ረሳን? ምድራዊ ጥያቄ ቀላል ነው ይታለፋል። አላህ ፊት ስንጠየቅ ምን እንላለን? መልስ አዘጋጁ። ውሃ ሰልችቶአችሁ በጀናባ የአላህን ገፀ-ምድር የምታበላሹ ሁሉ እኛን አይመለከትም አትበሉ ከርከሰት ታጠቡ ነው ምክራችን።

## ምዕራፍ ስምንት

### ስግደት (ሶላት)

የመታጠቡ አስፈላጊነት ለፀሎት መሆኑን ተግባብተናል። ታድያ ስግደት የሚገባው ለማን ይሆን? ለኢየሱስ፣ ለመንፈስ ቅዱስ፣ ወይስ ለአላህ (ለአብ)?

በዚህ ዙሪያ እንደ አማኞቹ አነጋገር ሦስቱን ሥላሴዎችን እናነጋግራለን። ቃላቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንከታተል፡-

<u>ኢየሱስ</u>

የማቴዎስ ወንጌል 4፥9 ሰይጣን ኢየሱስን ሲፈትነው፦ «ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው። ያን ጊዜ ኢየሱስ፦ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና አለው።»

ኢየሱስ ክብር ስግደት ለአላህ እንጂ ለራሳቸው እንኳ እንደማ ይገባ ለሰይጣን በመለሱት መልስ አረጋግጠናል። ኢየሱስ ስግደት የሚገባቸው ቢሆን ኖሮ ለራሴ ስገድልኝ ባሉ ነበር። ያሉት ግን ለአንድ አላህ ብቻ ስገድ ነው።

<u>መንፈስ ቅዱስ</u>

በሁለተኛ ደረጃ መንፈስ ቅዱስ 3ኛ አምላክ ነው የሚባለውን ለጊዜው ብቻውን ሳይሆን የተናገረው ከነጳውሎስ ጋር ስለሆነ እንከታተል።

በፍጡርና በፈጣሪ አላህ መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅና እርሱን ማገልገል ማምለክ ለርሱም ብቻ መስገድ ተገቢ ነው። ስግደት ለፍጡራን ከሆነ ግን ወንጀል መሆኑን መረዳት አለብን።

በተጨማሪም ወደ ሮሜ ሰዎች 1፥23 እንዲህ ይነበባል፡-

«የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ። ስለዚህ እርስ በርሳቸው ስጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩሰት

አኅልፈው ሰጣቸው ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ <u>በፈጣሪም</u> ፈንታ <u>የተፈጠረውን</u> ስለአመለኩና ስላገለገሉ ነው።»

እንዳያችሁት በመንፈሳዊ ጳውሎስ የተጻፈው ወንጌል አላህን ባለማምለክ አላህን ባለማገልገል የአላህን ሥልጣን ክብርና ስግደትን ለሰውና ለሌላ ፍጥረት አኅልፎ በመስጠታቸው እንደተወገዙና አላህ ለመጥፎ ነገር አኅልፎ እንደሰጣቸው በመንፈስ ቅዱስ ተናግሯል።

ኢየሱስ ፍጡር አይደለም ካላችሁ መ.ምሳሌ 8፥22 (በ1980 ቀለል ባለ አማርኛ የቀረበው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ኢየሱስ እግዚአብሔር ፈጠረኝ ይላልና። ያንብቡ።

የዮሐንስ ራዕይ 22:8 ላይ ያለው በተጨማሪ፦ ዮሐንስ፦ ለኢየሱስና ለመልአኩ ሊሰግድ ሲል ኢየሱስ እንዲህ ብሉታል «እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባርያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ»። ይላል። ታዲያ አምልኮና ስግደት የሚገቡት ለአንድ አምላክ ብቻ አይደለምን? መልሱን ለአንባቢያን ትተናል ።

## <u>እግዚአብሔር (አብ)</u>

በሦስተኛ ደረጃ እግዚአብሔር (አብ) ምን ይል ይሆን?

ትንቢተ ኢሳይያስ 45፥23 «ጉልበት ሁሉ ለኔ ይንበረከካል፥ ምላስም ሁሉ በኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ።» ይላል አምላክ። አዎ ጉልበት ሁሉ ለአላህ ይንበርከክ። የኛም ዓላማ ይህ ነው።

ኢየሱስም ስግደትና አምልኮ ይገባኛል አላሉም። መንፈስ ቅዱስም ስግደት ይገባኛል ብሉ አልተከራከረም። አላህም ክብሩን ሥልጣኑን አኅልፎ ለነሱ ስገዱላቸው የኔ ችግር የለውም አላለም። ክብር ስግደት ሁሉ፣ ጉልበት ሁሉ ለኔ ይንበረከካል ባይ ነውና ለርሱ ብቻ ይገባዋል ነው የምንለው። ስለዚህም ለርሱ ብቻ እንስገድ። እሱንም ብቻ እናምልክ።

ለሦስቱ አምላክ መገዛትም ትርፉ የቂያማ ቀን ትዝብት በመሆኑ እውነትን ሰምታችኋልና ለአላህ ብቻ ስገዱ እላችኋለሁ። አዳኝ ፈጣሪ ነውና፣ አምሳያና ተጋሪ የለውምና ብትጠሩት ይሰማችኋልና። እሱን (አብን) ብቻ አምልኩ፣ ስገዱለትም። ትድናላችሁ እላለሁ።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ቂብላ (የስግደት አቅጣጫ)

ብዙውን ጊዜ በኢስላም ላይ እንደ ትልቅ ጥያቄ የሚነሳው ወደ መካ ለምን ዞራችሁ ትሰግዳላችሁ? አቅጣጫ መምረጡ ለምን አስፈለገ? ወደዚህ ዙሩ ወደዚያ አትዙሩ የሚል ነገር እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ አልተናገረምና ሲሉ እሰማለሁ። እናንተም አጋጥሟችሁ ይሆናል።

እኔን ያጋጠመኝን ትንሽ ልንገራችሁ፦

የአርሲ ተወላጅና የዲፕሎማ ትምህርቱን አጠናቆ በላብራቶሪ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኝ የፕሮቴስታንት (ሙሉ ወንጌል) ሃይማኖት ተከታይ የነበረ ሰው ስለዚህ <u>ቂብላ</u> አጥብቆ ጠየቀኝ "ኢስላም የተሳሳተ ሃይማኖት መሆኑን እርግጠኛ የሆንኩት አቅጣጫ እየመረጣችሁ ስትሰግዱ ነው። ይህ ደግሞ በመጽሐፋችን የተጠላ ነው" አለ።

እኔም ትንሽ ጥያቄ አቀረብኩለት "ለመሆኑ በሙሴ ዘመንና ከሱ በፊት የነበሩ እስራኤላዊያን አማኞች እንደነበሩ ታውቃለህ?" አልኩት እሱም "አዎ ነበሩ" "ለመሆኑ የኃይማኖታቸውንስ ስም ታውቃለህ?" መልሱ "በርግጥ አላውቅም ክርስቲያን ሳይሆኑ አይቀሩም የሚል እምነት አለኝ" አለ በጥርጣሬ።

እኔም "ክርስትና ከክርስቶስ ወዲህ ነው ሙሴና ከሙሴ በፊት የነበሩ በሙሉ ታዛዦች ነበሩ። የሚታዘዙትም ለአላህ ነው እንጂ ክርስትና የለም አልኩት። በምሳሌ አስረዳሁት።

- አብርሃም ልጁን እንዲሰዋ በእግዚአብሔር ታዞ ትእዛዙን ለመፈፀም ወጣ (ታዛዥ ሆነ)።
- ሙሴም ወደ ፈርዖን ሳትፈራ ሂድ ተብሎ ታዘዘና ተቀብሎ ሄደ።
- ኖህ መርከብ ሥራ ተብሎ ሲታዘዝ ተቀበለና ሠራም።
- አደምና ሄዋንም ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉ ተብለው ታዘዙ ተባዙም።
- ኢየሱስም እራሱ አብ ትእዛዝ ሰጠኝ አለ ታዘዘም።

ታዲያ እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ታዛዥነታቸውን እውነት ነው ብለህ ታምናለህ?" አልኩት። "አዎ!" አለ ሳያመነታ። "አንተስ ለጌታህ <u>ታዛዥ</u> ነህ ወይ?" አልኩት። "አዎ" አለ። የሚገርመው ግን ሳያስብ ሙስሊም መሆኑ ነው። ግለትም ታዛዥ የሚለው የአማርኛ ቃል ወደ ዐረብኛ ሲተረጎም <u>ሙስሊም</u> የሚለውን ይተካልና። "ታድያ ከአደም ጀምሮ እስከ ዛሬ ምሽት የሚወለድ ሕፃን አንተንና ኢየሱስንም ጨምሮ ሙስሊሞች መሆናችሁን ታምናለህ ወይ? ታዛዦች ናችሁና"

አልኩት። ዐዋቂ ስለነበረ ተቀበለና ጎኝ ግን የስግደት አቅጣጫ የሚመርጠውን ሃይማኖት አልቀበልም" አለ። "በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ የስግደት አቅጣጫ ፍንጭ ቢኖርስ?" አልኩት ድምፁን ከፍ አደረገና እየሳቀ "አሁኑኑ ሸሃዳ ተቀብዬ ከናንተ ጋር በመስገድ የምትነግሩኝን ሁሉ እፈጽማለሁ" አለ።

በዚሁ ሐሳብ ከተግባባን በኋላ በፍጥነት መጽሐፍ ቅዱስን ከእጁ በመቀበል ከፍቼ እንዲያነብ ሰጠሁት። እንዲህ ይነባበል፦ 1 መጽሐፈ ነገሥት 8፥44 "ጠላቶቻቸውን ለመውጋት እንዲዘምቱ ሕዝብህን የምታዝበት ጊዜ በየትኛውም ስፍራ ሆነው ወደዚህች ወደ መረጥሃት ቤተ መቅደስ ፊታቸውን መልሰው በሚጸልዩበት ጊዜ በሰማይም ሆነህ ጸሉታቸውንና ልመናቸውን በመስማት ድልን አቀዳጃቸው።" (የ1980 መ.ቅ) ተጨማሪ አሪት ዘዳግም 12-11 በስሩው ያገኙታል።

ይህ ትንቢት በኢየሱስ ዘመንም እንዳልተፈጸመ ለማወቅ...

ዮሐንስ ወንጌል 4፥19 «ሴቲቱ፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ። አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፤ እናንተም ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አለችው። ኢየሱስም እንዲህ አላት፦ አንቺ ሴት እመኚኝ፥ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል።» "ይህ ጊዜ መቼ ይሆን?" አልኩት። ዝም አለ። የዚህን ማብራሪያ ከሱረቱል በቀራ ምዕራፍ 13 አነበብኩለት። ተግባባን።

ዶጋግዋ አንብቦ ከጨረሰ በኋላ መጽሐፉን ቁጭ አደረገና በሁለት እጁ ጉንጮቹን ደበባሰ። ከጥቂት ውይይት በኋላ ወዲያውኑ ሸሃዳ ተቀብሉ በአሁኑ ሰዓት በጠነከረ መልኩ የእስልምና ሃይማኖት በመከታተል ላይ ይገኛል። አላህ ጽናቱን ይስጠው በሉልኝ። እውነትን ለሚቀበሉ ሁሉ የአላህ ምሕረት ቅርባቸው ነውና።

እንባቢያን ሆይ! ኢየሱስ የተነበዩት ትንቢት ነው የተፈፀመው እንጂ ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ወደ አገሬ ዞራችሁ ስገዱ አላሉም። በኢየሱስ ያስተነበየውን ትንቢት አላህ በነቢዩ ሙሐመድ ﷺ አስፈጸመ። እርሳቸውም በአላህ ታዝዘው እኛንም አዘዙ እንጂ ቀደም ሲል ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ሴትየዋ እንዳለችው ወደ ኢየሩሳሌም (ቤተል መቅደስ) ይሰግዱ ነበር። በኋላም በአላህ ትእዛዝ ወደ መካ እንዲዞሩ ትእዛዝ ተሰጥቶአቸው በስግደት ላይ እያሉ ወደ መካ ዞሩ።

በዚያን ቀን ይሰግዱባት የነበረች ቦታ መዲና ስትሆን የመስጂዱ ስም መስጂደል ቂብለተይን (ባለ ሁለት ቂብላው /አቅጣጫው/ መስጂድ) ተብሎ ተሰይሞ እስከ ዛሬ በዚህ ስም በዓለም ዙሪያ ይታወቃል።

ተንኮል ቢኖርባቸውና እርሳቸው ብቻ የፈለጉት እምነት ቢሆን ኖሮ መጀመሪያውኑ ወደ ኢየሩሳሌም ባልዞሩ ነበር። ነገር ግን ይህ ትንቢት ወደፊት የሚፈፀም ነው ብለው የሚጠብቁም ክርስቲያኖች አልታጡም።

# ምዕራፍ አሥር

## የአሰጋገድ ሥርዓት

ማቴዎስ 26፥39 «ጥቂትም ወደፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ፦ አባቴ ቢቻልስ ይህች ጽዋ ከኔ ትለፍ፤» አለ። ይህም ሙስሊም በፊቱና በግንባሩ መሬት ነክቶ እንደሚሰግድ ማለት ነው። ይህን ያነሳነው በጸሎት ብቻ ጀነት ይገባል ስገደት አያስፈልግም። ከሆነም በግንባር መሬት አይነንካም የሚሉ ስላሉ ነው። ግንባራቸውም ለአምላክ መሬት እንዲነካ ነው።

በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 18፥42 ኤልያስ ራቱን በጉልበቱ መሐል አድርጎ ሰገደ ይላል።

ኢያሱ 5፥14 "ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ምድር ላይ ተደፍቶ ሰገደና..." ይላል። ሶላት መናሩን ተገበረ ማለት ነው።

በዚህ ከተግባባን በጋራ ተሰብስቦ መስገድ (ሶላቱል ጀማዓ) የሚባለው ይኖር ይሆን? እንመልከት።

መዝሙረ ዳዊት 96፥5 «ዳዊትም ኑ እንስገድ ብሎ ተጣራ» ይላል። ስለዚህ ተሰብስበን ለእግዚአብሔር ክብር እንስገድ። ኑ ተባብለን መስገድን (ሐያ ዐለ ሶላት)ን ለምን እንቃወማለን? ተሰባስቦ መስገድ በክቢዩ ሙሐመድ አልተጀመረምና። ገራ የገባን ሁሉ እንመለስ እላለሁ።

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

## የሴቶች ግዴታና መብት በእምነት

በሙስሊም ሕግ ሴት ለጸሎትም ሆነ ለሥራ ወደ ውጪ በምትወጣበት ጊዜ ሥርዓትን ተከትላ ባዝግታ ትናገር ይላል። መጽሐፍ ቅዱስስ ምን ይል ይሆን? እንከታተል።

ቆርንቶስ 14፥34 ሴት በአደባባይ አትናገር። ሙሉ ቃሉ እንዲህ ይነበባል፦«ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ። ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና። ለሴት በማኅበር መካከል መናገር ነውር ነውና፤ ምንም ሊማሩ ቢወዱ በቤታቸው ባሎቻቸውን ይጠይቁ፤ ምንው? የእግዚአብሔር ቃል የወጣ ከናንተ ነውን? ወይስ ወደናንተ ብቻ ደርሷል?» ይላል። ይህ ማለት አይመለከታችሁም ማለት ነውና ሰባኪ እህቶች...

የእስልምና ሃይማኖት ግን የሴት መብት እንደማንኛውም የእግዚ አብሔር (የአላህ) ፍጡር መከበር እንዳለበት ያረጋግጣል። እንደ ወንዶች ሁሉ ክቡር ፍጡራን መሆናቸውንም ያብራራል። ሌላው ቀርቶ የወለደ ችውን ልጅ ማጥባት የሚገዳት ከሆነ ባል ገንዘብ ከፍሎ በሌላ ሴት እንዲያስጠባላት ያዛል።

ከሁሉ በፊት ጤንነቷ እንዲጠበቅ ቅድሚያ በመስጠት፣ በአጠቃላይ ቤተሰባዊ ኑሮ ላይ ባሏን ሥርታ የማብላት ግዴታ እንደሌለባትና አቅም ከፈቀደ ደግሞ ቁጭ ብላ በማዘዝ እንድትኖር፣ ሠራተኛ እንዲቀጥርላትም ይፈቅዳል።

እስልምና አግባብ ያለውን ማንኛውንም ንግግርም እንድትናገርና እንድታስተምር የሚፈቅድላትና ከበታችነት ስሜትም እንድትወጣ የሚ ያደርግ እምነት እንጂ እንደ መጽሐፍ ቅዱሳችን ለወንድ እንዲገዙና የመናገር መብት እንዲያጡ አይፈቅድም። ነገር ግን ሥርዓት የሌለው አነጋገርንና ጋጠወጥ አለባበስን አጥብቆ ይቃወማል። ወሰን አልፈው ያለፈታድ እንዳይሄዱም ያስጠነቅቃል።

ይህ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ እና ተግባቢ ነው። ለምሳሌ ሴትና ወንድ ተፋጦ መተያየትን ከፋት ስላለው አምላክ ይህን አጥብቆ ከልክሏል። ሴት ፊቷን ትሸፈን ወንድም ዓይኑን ሰበር አድርጎ ይኑር ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ሐሳብ ላይ ድጋፉን ሲሰጥ እናያለን በማቴዎስ ወንጌል 5፥27 «አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከርሷ ጋር አመንዝሮአል። ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ መሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻላልና።" ይላል።

በዓይኑ ካየ የግድ መመኘቱ ስለማይቀር ነው። ዛሬ ግን ሴቶች ከወንዱ በበለጠ ደረጃ ዓይናቸውን አፍጥጠው በማየት በወንጌል ሰበካ ላይ ተሰማርተዋል። «ሴቶች ዝም ይበሉ» የሚለውን አንቀጽ አንብበው ይሥሩበት እንላለን።

የሚገርመው ግን ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንደ ሰነበተ ዘፈን ፋሽኑ ያለፈ ይመስል መጣሉ ነው።

ዓይኗን አፍጥጣ ወንድ ፊት ቆማ በመኪና ውስጥና መንገድ ላይ ወንጌል እሰብካለሁ ብላ ሕዝብ የምታስቸግር እህታችን ተሸክማ ያለችውን ቃል አንብባ ይሆን?

በተጨማሪም 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥9-14 «ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ። እግዚአ ብሔርን እንፈራለን ለሚሉት ሴቶች እንደሚገባ፥ መልካም በማድረግ እንጂ በሹሩባና በወርቅ ወይም በዕንቁ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለሙ። ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር፤ ሴት

ግን በዝግታ ትኑር፣ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሠለጥን አልፈቅድም። አዳም ቀድሞ ተፈጥሯልና፥ በኋላም ሔዋን ተፈጠረች፥ የተታለለም አዳም አይደለም፥ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች።»

ለመሆኑ ይህ የጳውሎስ ቃል ጡረታ እንደወጣ ባለሥልጣን ችላ መባሉ ለምን ይሆን? መቼ ይሆን ቃሉ የሚያገለግለው? በስህተት የገባ ቃል ስለሆነ ተጠላ አይባል የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነውና።

ይህን ጉድ ያላዩ እህቶቻችን ባዶ ፀጉራቸውን ሱሪ አድርገውና በዝግታ ሳይሆን በግርታ በወንድ ላይ በመሰልጠን የተገላቢጦሽ ወንዱ ዝምተኛ፣ ሴቱ ጉደኛ በመሆን የመጽሐፉን ትእዛዝ በተፃረረ አለባበስ መንፈስ ቅዱስ ተሞልተናል እያሉ ለስበካ አላስወጣ አላስገባ በማለት ያስቸገሩ እህቶቻችን አንድ ሊባሉ ይገባል።

የዘመናችን ፓሪ፣ ሊፕስቲክ፣ ቻፒስቲክ፣ የአፍንጫ ላይ ወርቅ በማድረግ፣ በመኳኳል፣ በአጠቃላይ እያሸበረቁና እየደመቁ፣ ለእሷህ ፍራቻ እራሳቸውን ዝቅ አድርገው ተሸፋፍና በኢማን በ(ሒጃብ) ተሸልመው በሚሄዱት ሙስሊም እህቶቻችን ላይ ያፌዛሉ።

እነኚህ ስልጡናች የዘመኑ የሰይጣን ኮርቻ ሆነው የምናያቸው አልማዞች ይህንን ቃል አላዩም እንዳንል አይተዋል። አይተዋል እንዳንል አላዩም። እንዳው ዝም ሆኗልና አላህ እውቀቱን ይሸልማቸው።

1ኛ ቆሮንቶስ 11፥5 እንዲህ ይላል፦«ራስዋን ሳትሸፍን የምትጸልይ ሴት ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን ታዋርዳለች፣ እንደተላጨች ያህል አንድ ነውና። ሴትም ራስዋን ባትሸፍን ጠጉርዋን ደግሞ ትቆረጥ፣ ለሴት ግን ጠጉርዋን መቆረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፍን» ይላል።

ይታያችሁ ይህን የሚያከል የሒጃብ (የመሸፈን) ግዴታ ተጽፎ እያለ እያየን እያነበብን የጌታን ቃል ለማሟላት የሚሸፈኑትን ሙስሊም ሴቶችን እፋችንን ሞልተን ስንተቻቸው ትንሽ እንኳን የተሳሳትን አይመስለንም። እነሱ ግን የቃሉ ፈጻሚዎች ናቸው እንጂ የቁንጅና ተወዳዳሪዎች አይደሉም። አላህ ይውደዳቸውና።

እስቲ አንድ ገጠመኝ ልንገራችሁ፦ በአንድ ወቅት ከአዲስ አበባ ወደ ሻሸመኔ ከተማ በሚሄድ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ተሳፍረን ስንጓዝ አንዲት ሴት ከፊት ወንበር ላይ ጂንስ ሱሪ ለብሳና አጠር ያለውን ፀጉሯን በጎን ለቀቅ አድርጋ በበጋ ተዘርግቶ የተጎሳቆለ ቦቆሉ የመሰለ ቡናማ ፀጉሯን ግራ ቀኝ እያወናጨፈች ፊቷን ወደ ኋላ ማለትም ወደ ሕዝቡ በማዞር የወንጌልን ስበካ በሰፊው ተያያዘች።

በዚህ መኪና ውስጥ ያሉት ሰዎች አብዛኛዎቹ አዛውንትና በዕድሜ በጣም የገፉ አንቱ የሚባሉ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። ተሳፋሪዎቹን ስመለከት አትኩሮ ይመለከቷታል። አብዛኛው ሰው በጥላቻ

ያጉረመርማል። ነገር ግን ደፍሮ ዝም በይ! ያለት የለም። ከግራ ቀኝ ጉኗ ቁጭ ቁጭ ያሉ ወጣቶች የሚነካት ወንድ ካለ! የሚሉ ይመስላሉ። በዚህ የተቀጣጠለ ንግግሯና ማቆሚያ ያለው በማይመስል ስበካዋ የተሰላቸ ተሳፋሪ ተስፋ ወደ መቁረጥ ሲቃረብ አላህ አንድ ነገር አመላከተኝ። "እህቴ ይቅርታ! አንድ ትንሽ ጥያቄ ብጠይቅሽ ፍቃደኛ ነሽ ወይ?" አልኳት። አናጋሪ ያጣች ወጣት በደስታ "አዎ፣ ጠይቅ" ብላ ኮራ ባለ አንደበት ፍቃደኝነቷን ገለጠችልኝ። አንድ ጊዜ በመኪናው ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ እንዲሰማኝ በአክብሮት ተማጸንኩኝ። ሁሉም ፍቃደኛ ነበርና ፀጥታ ሰፈነ።

ወዲያውኑ ትንሽ ማሳሰቢያ ለቤቱ ተናገርኩኝ። "እህታችን ወንጌል እየሰበከች (እያስተማረች) ስለሆነ ያልገባኝን ጥያቄ እንድጠይቃት ከቤቱ ይፈቀድልኝ" አልኩኝ። ተሳፋሪዎቹም ሳያመነቱ በደስታ "ኧረ እሺ ጠይቅ" አሉኝ። ቀጠልኩኝና "እህቴ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሙሉ እምነት አለሽ?" "አዎ!" "እሺ 1ኛ ቆሮንቶስ 14:34ን ሁላችንም እንድ ንሰማ ድምጽሽን ከፍ አድርገሽ አንብቢ እስቲ" አልኳት። ወዲያውኑ ብድግ ብላ ማንበቧን ቀጠለች። እንዲህ በማለት፦ "<u>ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ፤ ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና።"</u> የሚለውን ንባብ በጀመረችበት ደቂቃ ውስጥ ሕዝቡ ሳቅ የተቀላቀለበት ጩኸት በጆሮዋ ላይ አቀለጠ። እንደቆመች ለ2 ደቂቃ ያህል ተሳቀባት። ቀይ የነበረ ፊቷ ቀስ በቀስ እየጠቆረ መጣ፤ አቀረቀረች። ለመናገር ስትፈልግ የሕዝቡ ሳቅ ጊዜ ከለከላት። እራሷን በራሷ በመስደቧ ተፀፀተች። እኔም ተሳፋሪው በሙሉ ከጥቂት ሰው በስተቀር ደስተኛ ነበርን። ዝዋይ ስንደርስ ምሳ ከበላን በኋላ አላህን አመሰገንኩኝ። አናጋሪ እሱ ነውና (አልሐምዱ ሊሏህ ረቢል ዓለሚን)። ከዝዋይ በኋላ እህታችን ጥሩ ጨዋ ሆና ሻሸመኔ ገባን። ሲጠሩአት እንኳ አቤት አትልም ነበር።

ሻሸመኔ ደርሰን ስንወርድ «ወንድም! ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለህ ወይ?» ብላ በጣም በቀዘቀዘ ድምጽ ጠየቀችኝ። የሚከተለውን ጽፌ ሰጠኋት። ኦሪት ዘዳግም 22፥5 «ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ፥ ወንድም የሴት ልብስ አይልበስ፤ ይህን የሚያደርግ በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነውና።» የሚለውን ካነበበች በኋላ እየሳቀች እራሷን ነቅንቃ በመገረም ተለያየን። ሱሪ አድርጋ ነበርና መሳሳቷን የተረዳች መሰለኝ። አላህ ያሳውቃት። ከጥመትም ይመልሳት። ሱሪ አስወልቆ ቀሚስ ያልብሳት እላለሁ።

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ብቻ ተዋጉ ወይስ ሌሎችም ነቢያት?

ብዙውን ጊዜ የእስልምና ሃይማኖት የተስፋፋው በሰላም ሳይሆን በጦርነት ነው፣ በሰላም ቢሆን ኖሮ ውጊያ (ጂሃድ) ባላስፈለገ ነበር፣ እግዚአብሔር ጦረኛ አይደለም ፍቅር ነውና ሲባል እሰማለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ዙሪያ ምን ይለን ይሆን? ከዚያ በፊት ግን ስለ ጂሃድ ሊታወቅ የሚገባ አንድ ጉዳይ አለ ይኸውም ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ የተዋጉት እስልምናን በግድ ለማስፋፋት ሳይሆን በርሳቸውና በተከታዮቻቸው ላይ የተሰነዘረ ጥቃትና ወረራን ለመከላከል ብቻ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። የመከላከል ጦርነት በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቅዱስ ቁርአን የተደገፈ ነው።

ኦሪት ዘዳግም 20:4-14 «ከናንተ ጋር የሚሄድ፣ ያድናችሁም ዘንድ ጠላቶቻችሁን ስለ እናንተ የሚዋጋ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነውና። ...በርስዋ ያሉትን ወንዶች ሁሉ በሰይፍ ስለት ትገድላቸዋለህ።»

ይህ አንቀጽ በአጭሩ የተጻፈው ነውና ሙሉ ሐሳቡን ከመጽሐፍ ቅዱስ ታገኛላችሁ። ሙሴን ተዋጋ ያለው (ያዘዘው) አላህ ነቢዩ ሙሐመድንም ﷺ አዘዘ እንጂ በፍላጐታቸው ተነስተው ለዝናቸው አልተዋጉም።

መጽሐፈ ኢያሱ 8፣18፡- «እግዚአብሔር ኢያሱን፡- ጋይን በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁና በእጅህ ያለውን ጦር በላይዋ ዘርጋ አለው፤ ኢያሱም በእጁ ያለውን ጦር በከተማይቱ ላይ ዘረጋ።....»

ትንቢተ ኤርምያስ 11:22፡- «ጎበዛዝቶቻቸው በሰይፍ ይሞታሉ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውም በራብ ይሞታሉ» ተብሎ የተተነበየው ትንቢት እንጂ ነቢዩን ሰይፍ ያስመዘዛቸው ፍላጎታቸውን ለማሟላት ከገዛ ጎሳቸው ጋር አልተጋጩም።

አባት እናት ሃብት ንብረት የሌለው ነቢይ በጉልበቱ ተማምኖ ወይም በዘመድ ወገኑ ተመክቶ አልተነሣም፣ የተመካው ግን በአላህ ነበርና ያሰበውን አደረገለት።

ስለ እምነቱ እውቀት ያነሰው ሰው በጦርነት የመጣ የዐረብ ሃይማኖት ነው እስልምና ይላል። ሳትታዘዙ አልቀራችሁም። እውነትነቱን ያወቁ ግን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች በደብዳቤ ብቻ እስልምናን ተቀብለዋል። በዚህ የተነሳ ኢትዮጵያ በዓለም ሙስሊም ዘንድ ከፍተኛ ውዴታና ከበሬታ አላት። የዐረብ ሃይማኖት ቢሆን ኖሮ ከዐረብ ጋር

ምን አጣላቸው? ከገዛ ዘመዶቻቸውና አጎታቸው ጋር የተዋጉት ነቢዩ ባሕላችሁን እናስፋፋ ብለው ሳይሆን ባሕላችሁን ትታችሁ የአላህን እምነት ያዙ ነው። የአላህ እምነት ባይሆን ኖሮ ከገዛ አገራቸው ባልተሰደዱ ነበር። በውሸትም ቢነሱ ባላሸነፉም ነበር። እውነት አሸናፊ ናትና አሸነፉ። በሃይማኖት ግን ፈጽሞ ማስገደድ ከልክል መሆኑን በቅዱስ ቁርአን 2፥56 ይመልከቱ።

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት

## እውነተኛ አምላክ ማነው?

## ባሕሪውስ እንዴት ነው?

በዛሬይቱ የተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ላይ የተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች የአምላካቸውን ስም በተለያየ ዓይነት ስያሜ ይጠሩታል። ለምሣሌ ኢትዮጵያዊያን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር፣ የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ ይሖዋ፣ ሙስሊሙ ዓለምና ክርስቲያን ዐረቦች ደግሞ አላህ በማለት ይጠሩታል። እርግጥ ነው አምላክን በተለያየ ዓይነት ስያሜ ብንጠራውም ይሰማናል። ምክንያቱም ቀድሞውኑ ቋንቋዎችን ለያይቶ ፈጥሮአልና። አላህ እንዲህ ይላል፦
«ሰማያትንና ምድርን መፍጠሩ፣ የቋንቋዎቻችሁና የመልኮቻችሁ መለያየት ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው።» አል-ሩም ፡ 22

ይሁን እንጂ ሁሉም ስያሜዎች አምላክን ያመለክታሉ ማለት ነውን? አይደለም። ለምሳሌ ያህል እግዚአብሔር እና አላህ የስም ልዩነት ነው እንጂ ሁለቱም አንድ ናቸው የሚል አመለካከት በብዙ ሰዎች ዘንድ አለ። ይህ በእርግጥ ምን ያህል እውነት ነው? በነቢዩ ሐዲስ በቁርአንና በክርስቲያኖች መጽሐፍ ላይ ተንተርሶ የሚቀርበውን የሚከተለውን ጥቅስ በማገናዘብ የፈጣሪዎን ማንነት ይወቁ፦

<u>1) ፈጣሪ ሁሉን ዐዋቂ ነው።</u>
«የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው፣ ከእርሱም በቀር ማንም አያውቃቸውም፣ በየብስና በባሕር ያለውንም ሁሉ ያውቃል፣ ከቅጠልም አንዲትም አትረግፍም እርሱ የሚያውቃት ቢሆን እንጂ...»

አል-አንዓም፡ 59

«ሰዎች ሆይ ቃላችሁን መስጥሩ (በሚስጥር ተናገሩ) ወይም በርሱ ጩኹ፥ እርሱ (አላህ) በልቦች ውስጥ ያለን ሁሉ ዐዋቂ ነው»

አል ሙልክ ፡13

ከአንቀጾቹ እንደምንረዳው 'አላህ' ከርሱ ሊሰወርና ሊደበቅ የሚችል ነገር እንደሌለና ሰው ነገ ከነገ ወዲያ የሚናገረውን አስቀድሞ የሚያውቅ መሆኑን ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል፡-

«የሰዶምና የገሞራ ሕዝብ የሚፈጽሙትን በደል ሰምቻለሁ፤ ኃጢአታ ቸውም እጅግ ከባድ ነው፤ ስለ እነርሱ የሰማሁት ነገር ሁሉ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ወደ እነርሱ እወርዳለሁ» ኦሪት ዘፍጥረት ምዕ.18 ቁ.20-21(ቀለል ያለ አማርኛ ትርጉም)።

እግዚአብሔር 'ሶዶምና ገሞራ' ኃጢአት እንደሚሠሩ ሰምቶ ነበር ይሁን እንጂ የሰማው ነገር እውነት ይሁን አይሁን ሄዶ ማረጋገጥ ግድ ሆኖበታል። ማየት ማመን ነውና! ይህ የፈጣሪ ባሕሪ ነውን?

## 2) ፈጣሪ ሰዎችን ወደጥሩ ነገር የሚመራ ነው።

«ዝሙትንም አትቅረቡ እርሱ በእርግጥ መጥፎ ሥራ ነውና፣ መንገድነቱም ከፋ!» አል-ኢስራእ : 32

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ፣ ቁማርም ጣዖታትም፣ የመጠንቆያ እንጨቶችም ከሰይጣን ሥራ የሆኑ ርኩስ ብቻ ናቸው፣ ርኩሱንም ራቁት ልትድኑ ይከጀላልና» አል-ማኢዳህ 90

ዝሙት፣ መጠጥ፣ ቁማርና ጣዖታት ምን ያህል ለሰው ልጆች ጉጂ እንደሆኑ ከሁላችንም የተሰወረ አይደለም። ሰው ግን ከዚህ ሱስ ሊላቀቅ አልቻለም። አንደኛው ምክንያት ከጉጂ ነገሮች ራቁ የሚለውን የቅዱስ ቁርአን ትምህርት እሺ ብሎ ባለመቀበሉና ሌላኛው ደግሞ፡-

«ለጥፋት ለቀረበው ሰው ብርቱ መጠጥ ስጡት፥ ነፍሱ ለመረረው የወይን ጠጅ ስጡት፤ ይጠጣ ድህነቱንም ይርሳ ጉስቁልናውንም ከእንግ ዲህ ወዲህ አያስብ» መጽሐፈ ምሳሌ ምዕ. 3፤6-7

«እግዚአብሔር በሆሴዕ አማካይነት ለእስራኤል ሕዝብ ቃሉን ማስተ ላለፍ ሲጀምር ሆሴዕን እንዲህ አለው፡- ሕዝቤ ከእኔ ተለይቶ አጸያፊ የሆነ የዝሙት ሥራ በመሥራት ላይ ይገኛል። እንግዲህ አንተም ሂድና ዘማዊት ሴት አግባ እንደ እርስዋም ሴሰኞች የሆኑ ልጆችንም ከእርስዋ ውለድ አለው» (ቀለል ያለ የአማርኛ ትርጉም) ትንቢተ ሆሴዕ 1፤2 የሚለውን ጥቅስ አምነው በመቀበላቸው ነው። ፈጣሪ መጠጥንና ዝሙትን እንዴት ይፈቅዳል?

## 3) ፈጣሪ ሚስትንና ልጅን ከመያዝ የጠራ ነው

«አልረሕማን ልጅን ያዘ (ወለደ) አሉ፤ በእርግጥም ከባድ መጥፎን ነገር አመጣችሁ፤ ከእርሱ (ከንግግራቸው) ሰማያት ሊቀደዱ፣ ምድርም ልትሰነጣጠቅ፣ ጋራዎችም ተንደው ሊወድቁ ይቃረባሉ። ለአልረሕማን

ልጅ አለው ስለአሉ። አልረሕማን ልጅን መያዝ አይገባውም። በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ በትንሳኤ ቀን፣ ለአልረሕማን ባሪያ ሆነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም።» መርየም 88-90

የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ግን:-
"እኔ ለእስራኤል አባት ነኝና ኤፍሬምም በኩሬ (የመጀመሪያ ልጄ) ነውና..." ትንቢት ኤርሚያስ ምዕ 31፥9

ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ ተብሏል። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3፥16 ላይ።

የሰው ልጅ አእምሮ ሊቀበል የሚችለው ከአፍሪካ የተወለደ ልጅ አፍሪካዊ፣ የቻይናው ቻይናዊ፣ የሕንዱ ደግሞ ሕንዳዊ፣ መምሰሉን ነው። የአምላክ ልጅ ደግሞ አምላክን መምሰል አለበት። የዚህ ብቸኛ የፈጣሪ ልጅ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምስልና ቅጅዎቹ በአያሌ ሰዎች ዘንድ ይገኛሉ። Jesus of Nazareth or King of Kings ተብለው በሚጠሩት ፊልም ላይ ኢየሱስም ሆነ የሠራውን ተዋናይ ጀፈሪ ሀተሪን ስንመለከት የክርስቲያኖቹ አዳኝ ዞማ ፀጉሩ፣ ሰማያዊ ዓይኑ፣ ሰልካካ አፍንጫው ከቆንጆ ቁመናው ጋር ከአይሁዳዊ ይልቅ ጀርመናዊ ይመስላል።

በእርግጥ ልጅ ነጭ ከሆነ አባትም ነጭ (አምላክ) ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ በምድረ ገጽ የሚገኙት ጥቁር ዘሮች ሁሉ ሳያውቁት የአምላክ የእንጀራ ልጆች እንደሆኑ ስለሚሰማቸው የበታችነት ስሜት ከነፍሳቸው ጋር ተዋህዷል።

ምንም ያህል የፊት የቆዳና የፀጉር አለስላሽ ቅባቶች ቢወስዱም ይህንን የበታችነት ስሜት ከቶውኑም ሊያጠፉት አይችሉም። እንደ ሙስሊሞች አመለካከት አምላክ ነጭም ጥቁርም፣ ሚስትና ልጅም የለውም። የሰው ልጅ አእምሮ ሊያስበው ከሚችለው በላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን:- የእግዚአብሔርም ቃል ወደ ሕዝቅኤል እንዲህ ሲል መጣ:- «የሰው ልጅ ሆይ! ከአንድ እናት የሚወለዱ ሁለት እኅትማማቾች ነበሩ፤ እነርሱም በወጣትነታቸው ወራት በግብጽ ሲኖሩ ክብርናቸውን አጥተው በመዋረድ አመንዝሮች ሆኑ። ከእነርሱም ታላቂቱ ኦሆላ ትባል ነበር፤ የምትወክለውም ሰማርያን ነው፤ ታናሺቱ ደግሞ ኦሆሊባ ትባል ነበር፤ የምትወክለውም ኢየሩሳሌምን ነው፤ እኔ ሁለቱንም አገብቼ ልጆች ወለዱልኝ»። ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕ.23 ከቁ.2-5. (ቀለል ያለ አማርኛ መ.ቅ.)። መውለድና ሚስት ማግባት የፈጣሪ ባሕሪ ነውን?

## 4) ፈጣሪ ሰዎችን አይበድልም:-

«አላህ ሰዎችን ምንም አይበድልም ግን ሰዎች ነፍሶቻቸውን ይበድላሉ።»
ዩኑስ : 44

የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል፦

«ዲቃላ ሆና የተወለደ ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ አይግባ፤» ኦሪት ዘዳግም ምዕ. 23 ቁ. 2

በመሠረቱ ዲቃላ የሚባለው ሁላችንም እንደምናውቀው ኃጢአተኞቹ ሴቲቱና ወንዱ እንጂ የተወለደው ሕጻን እንዳልሆነ ነው። እግዚአብሔር ግን ወደ እርሱ ጉባዔ እንዳይመጣ የከለከለው የተወለደውን ሕጻን እንጂ ዝሙተኞቹን አይደለም። ይህ በደል አይደለምን?

## <u>5) ፈጣሪ ማንንም አይመስልም፦</u>

«እርሱን የሚመስለው ምንም ነገር የለም» አል-ሹራ :11

«ለአላህ አምሳያዎችን አታድርጉ አላህ መሣይ እንደሌለው ያውቃል እናንተ ግን አታውቁም» አል-ነሕል፥ 74

የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ግን

«ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክና በራሱ አምሣያ ፈጠረው» ኦሪት ዘፍጥረት 1፥27

## <u>6) ፈጣሪ በማንም አይታይም፦</u>

«ዓይኖች አያገኙትም (አያዩትም) እርሱ ግን ዓይኖችን ያያል፤ እርሱም ርህራሄው ረቂቁ ውስጠ ዐዋቂው ነው።» አል-አንዓም : 103

ከአንቀጹ እንደምንረዳው ኃያሉ አምላክ አላህ በማንም ሊታይ እንደማይችል ነው። ይሁን እንጂ፦

«ሙሳም ለቀጠሮአችን በመጣና ጌታውም ባነጋገረው ጊዜ ጌታዬ ሆይ! (ነፍስህን) አሳየኝ፥ ወደ አንተ እመለከታለሁና አለ፤ (አላህም)፦ በፍጹም አታየኝም። ግን ወደ ተራራው ተመልከት በሥፍራውም ቢረጋ በእርግጥ ታየኛለህ አለው። ጌታውም ለተራራው በተገለጸ ጊዜ ንኩትኩት አደረገው፤ ሙሳም ጮሆ ወደቀ፤ በአንሰራራም ጊዜ ጥራት ይገባህ፥ ወደ አንተ ተመለስኩ፤ እኔም (በወቅቱ) የምእመናን መጀመሪያ ነኝ አለ።» አል-አዕራፍ : 143

አዎ! የአላህ የአምላካችንን ብርሃን እንኳን ሰው ተራራም ቢሆን መቋቋም እንደማይችል ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ግን፦

«ከፍ ባለና ረጅም ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት» ትንቢተ ኢሣያስ 6፥1

«ያዕቆብም እኔ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አይቼ እነሆ በሕይወት እገኛለሁ አለ።» ኦሪት ዘፍጥረት 32:30

«እርሱ ሙሴ እኔን በግልጽ አይቶኛል» ዘኁልቁ 12፥8 (1980 ቀለል ያለ የአማርኛ ትርጉም)

## 7) አምላክ ራሱ እውነት ነው፤ የሚናገረውም እውነት ነው፡-

«ይህ፤ አላህ እርሱ እውነት በመሆኑ ከእርሱም ሌላ የሚገዙት ነገር እርሱ ፍጹም ውሸት በመሆኑ አላህም እርሱ የሁሉ በላይ ታላቅ በመሆኑ ነው።» አል-ሐጅ፥ 62

«አላህ ከእርሱ በቀር አምላክ የለም፥ ወደ ትንሣኤ ቀን በእርሱ ጥርጥር የሌለበት ሲሆን በእርግጥ ይሰበስባችኋል፤ በንግግርም ከአላህ ይበልጥ እውነተኛ ማነው?» አል -ኒሳእ ፥ 8

«ይህ፤ አላህ እርሱ እውነት፤ ከእርሱም ሌላ የሚገዙ (ጣዖት) ውሸት በመሆኑ፤ አላህም እርሱ የበላይ ታላቅ በመሆኑ ነው።» ሉቅማን ፥ 30

የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ግን፡-

«ነቢዩም ቢታለል ቃልንም ቢናገር ያንን ነቢይ ያታለልኩ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።» ትንቢተ ሕዝቅኤል 14፥9

አምላክ ነቢይ እንዲያታልል ያደርጋልን?

## 8) የአምላክ ባሕሪ

«አላህ ከእርሱ በቀር አምላክ የለም፤ ሕያው ራሱን ቻይ ነው፤ ማንገላጀትም ሆነ እንቅልፍ አትይዘውም፥» አል-በቀራህ፥255

የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ግን፡-

«በመጨረሻም እግዚአብሔር ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ተነሣ፤ የወይን ጠጅም ጠጥቶ ድፍረት እንደሚሰማው ጀግና ሆነ፤» መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 78፥65

## መልስ የሚሹ ጥያቄዎች

«ፈጣሪሽ ባልሽ ነው ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው።»

ትንቢተ ኢሳያስ 54፥5

እግዚአብሔር ሚስት አለው ወይ ?

«በዚያም ቀን እግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጉር ይላጨዋል፤ ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላል።» ትንቢተ ኢሣያስ 7፥20

ምላጭ መከራየትና ጺምና ፀጉርን መላጨት ከአምላክ ባሕሪ ጋር ይሄዳል ወይ?

«የእግዚአብሔርም መንፈስ በላዩ (በሳምሶን) በኃይል ወረደ፤ ወደ አስቀሎናም ወርዶ፥ ከዚያም ሠላሳ ሰዎችን ገደለ፥ ልብሳቸውን እንቆቅልሹን ለፈቱት ሰዎች ሰጠ።» መጽሐፈ መሣፍንት 14፥19-20

ከዚህ ታሪክ እንደምንረዳው ሳምሶን ከዕለታት አንድ ቀን ባደረገው ሠርግ ሠላሣ የፍልስጤም ወጣቶች ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ተልከውለት ነበር። ሳምሶንም እነዚህን ሰዎች እንዲህ አላቸው፦ አንድ እንቆቅልሽ ልጠይቃችሁ በሰባት ቀን ውስጥ ከመለሳችሁ ሠላሰ ቅያሪ ልብስና የበፍታ ቀሚስ ትሰጡኛላችሁ። ይሄ ደግሞ የቁማር ጫወታ መሆኑ ግልጽ ነው። ሰዎቹም በጥያቄው ተስማምተው ሄዱ እስከ አራት ቀን ድረስ መልሱን ሊያገኙ አልቻሉም።

ግን አንድ ሐሳብ መጣላቸው ብሳምሶን ሚስት በኩል መልሱን ማግኘት። ስለሆነም ሚስትየውን ባሏን ጠይቃ መልሱን ይዛ ካላመጣች ከነባሏ ቤቱን በእሳት እናጋያለን ብለው አስፈራሯት። ሚስትየውም ባሏ እግር ላይ ወድቃ እያለቀሰች የእንቆቅልሹን መልስ ጠየቀችው። እርሱም በሰባተኛው ቀን ነገራትና ሄዳ ለሰዎቹ ነገረቻቸው። እነርሱም ፀሐይ ሳትጠልቅ ቶሎ መጥተው መልሱን ነገሩት። ሳምሶንም እንዲህ አላቸው፦"በእኔ ጊደር ባታርሱ ኖሮ መልሱን ባላገኛችሁት ነበር" ይህም በኔ ሚስት ተጠቅማችሁ መልሱን አገኛታችሁታል ማለቱ ነው።

እንግዲሀ ጥያቄው ተመልሷል። ሳምሶን ማድረግ ያለበት ነገር ቢኖር የገባውን ቃልኪዳን መሙላት ብቻ ነው። ሠላሳ ልብስ እንዳይብ ጣቸው የለውም። የገድ ሰላሣ ልብስ ለማግኘት ሠላሳ ሰው መገደል ነበረበት። እራሱን ሲያይ ደግሞ አንድ ሰው ነው። እንዴት አድርጐ ሠላሳ ሰው ይገደል? ያውም በቁማር ጨዋታ መሀል።

በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር የረዳው። ሙስሊሞች እንደሚያምኑትና በቅዱስ ቁርአንም እንደተገለጸው አል-ሙጃደለህ፡ 22 ላይ አላህ መንፈሱን የሚያበረታታው በርሱና በትንሣኤ ቀን ላመኑት ብቻ ነው እንጂ ቁማር ተጫውተው የሰውን ሕይወት ማጥፋት በሚፈልጉት ላይ አይደለም። ምክንያቱም እርሱ መጥፎ ነገርን አያዝምና። አላህ እንዲህ ይላል፦

«መጥፎንም ሥራ በሠሩ ጊዜ፡-በርሷ ላይ አባቶቻችንን አገኘን፥ አላህም በርሷ አዞናል ይላሉ፤ አላህ በመጥፎ ነገር አያዝም፥ በአላህ ላይ የማታውቁትን ትናገራላችሁን? በላቸው።» አል-አዕራፍ ፡ 28

# የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በአጭሩ ሲብራራ

1. እውነተኛ አምላክ አላህ ብቻ ነው፦
«ይኸም እውነተኛ ጌታችሁ አላህ ብቻ ነው፣ ከእውነትም ሌላ ጥመት እንጂ ሌላ ምን አለ?» ዩኑስ ፡ 32

2. እውነተኛው ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው። «ከእስልምና ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ከእርሱ ፈጽሞ ተቀባይ የለውም፣ እርሱም በመጨረሻይቱ አገር ከከሳሪዎቹ ነው።» አሊ ዒምራን፡ 85

3. እውነተኛ መጽሐፍ ቁርአን ብቻ ነው ፦
«ይህን ቁርአን በተራራ ላይ ባወረድነው ኖሮ ከአላህ ፍራቻ የተነሳ ተሰንጣቂ ሆኖ ባየኸው ነበር» አል-ሐሽር ፡ 21

4. የነቢያት መደምደሚያ ሙሐመድ ﷺ ብቻ ናቸው፦
«ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፣ ግን የአላህ መልዕክተኛና የነቢያቶች መደምደሚያ ነው።» አል-አሕዛብ፡ 40

5. ይህችን አነስተኛ ጽሑፍ በደንብ ያነብቧትና እውነተኛ አምላክዎን ይወቁት። ምናልባት እስካሁን አላህን አላመለኩ እንደሆነ ኃጢአትዎን ሊምር ዝግጁ መሆኑን እንዲህ በማለት ይገልጽልዎታል፦
«እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ አላህ ኃጢአቶችን በመላ ይምራልና።» አል-ዙመር፡ 53

ስለሆነም ቶሎ ብለው ወደ እስልምና ይግቡ። «ሁሉንም ፈትኑ መልካሙንም ያዙ።» በሚቀጥለው ጽሑፌ እስከምንገናኝ አላህ ሰላምና እድሜ ይስጠን፣ ከስጋትም ይጠብቀን እላለሁ።

*ሠላም ቅንን መንገድ በተከተለ ላይ ይሁን ።*

# ማን ይሞክር?
## *ማርቆስ 16 :16*

ማርቆስ 16 ላይ ወንጌሉ ተከፍቶ
ክርስቲያን ሙስሊምን ለውይይት ጠርቶ
አንድ ቀን ጉድ ታየ በአደባባይ ወጥቶ
ለጥ ባለ ሜዳ ሰው ተመቻችቶ
እውነተኛን መጽሐፍ ለማወቅ ታስቦ
ሲታይ ያምር ነበር ሕዝብ ተሰብስቦ
ውጤቱን ለመስማት ሁሉም እየጓጓ
መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ ቁርአን ዛሬ የሚያስጋ
ስንቱ ገደል ገባ ስኳርን ፍለጋ
ትንሽም ሳይቆይ ወዲያው ተጀመረ
ክርክሩ ይሁን ዉጤቱ ያማረ
ሜዳው ተጣበበ ሕዝቡ እየጨመረ
ሙስሊምን በመወከል እኔ ተመድቤ
ስመታም ችያለሁ እንኳን ተሰድቤ
የነሷራ ወኪል ብቅ አለ ደርቤ
እውነት አሸናፊ ናት አውቃለሁ በልቤ
ዋሒዱል ቀሃርም ነበረ አጠገቤ
የውይይት ርእስ ሲመረጥ ከቤቱ
ነሷራና ሙስሊም ዋና ልዩነቱ
አልዋጥ ብሎን ነው ዒሳ ጌትነቱ
በኢየሱስ ያመነ ጀነትን መግባቱ
አንድነቱ ቀርቶ አምላክ ሦስትነቱ
ሰው እየከፈረ በቀን በሌሊቱ
ቶሎ ጀምሩልን ይሰማ ውጤቱ
ያመነ የተጠመቀ
ከኃጢአት ሁሉ በእውነት የራቀ
ሰይጣንን ያወጣል ምንም ሳይቸግረው
አዲስ ቋንቋ ይፈጥራል ምንም አይበግረው
እባብን ይይዛል ከነሕይወቱ

ይህ ብቻም አይደለም ተአምር መሥራቱ
መርዝ እንኳ ቢጠጡ አማኞች አይሞቱ
ብሉ ተናገረ ማርቆስ በመልዕክቱ
እስከዚህ ድረስ ነው የአማኝ ብርታቱ
ሁሌ ያሸንፋል ኢየሱስ ጌትነቱ
ኢየሱስን አምልኩ እንዳትሳሳቱ
ይህን ለማጣራት ማርቆስን ከፈቱ
ብሉ ሲያበቃ ተራውን ደርቤ
ማላታይን ገዛሁ ልሰጠው አስቤ
በኢየሱስ ያመነ መርዝ እንኳ ቢጠጣ
አይሞትም ብለሃል ይኸው እንካ ጠጣ
ይህን ብዬ ስለው መልሶ ተቆጣ
አንስቼ ብሰጠው መርዙን ለደርቤ
እያየሁ አልሞትም አንሳ ካጠገቤ
አነበብኩኝ እንጂ አላምንም ከልቤ
ሰድቦኝ ፈትለክ አለ ጉበዙ ደርቤ
ውሸት ተጋለጠ እኔ ተሰድቤ
ዞር ብዬ ባየው የለም ካጠገቤ
ግራ ተጋባና አማኝ በዕለቱ
መርዝ እንኳ ቢጠጡ ጴንጤዎች አይሞቱ
ትንሿ ብርሌ ማላታይን ይዛ
አንድ ብር ብቻ ናት ከሱቅ ስትገዛ
ሰዓትም አትፈጅ ለማድረግ ጀናዛ
ለመስጠት ስሞክር ወዲያው ለደርቤ
መድረክ ለቆ ኖሮ የለም ካጠገቤ
ማን ይሞክር ብዬ ደጋግሜ ብጣራ
መርዝ የሚጠጣ ከቶም የለም ፋራ
ብሉ ሰደበኝ ጎበዙ ደርቤ
አገር ቀየረና አሁን ገባ ሮቤ
በሙስሊሙ አሸናፊነት አበቃ ክርክር
ዛሬም ይቻትና መርዟን ማን ይሞክር?


## እንግባ ቶሎ

ሳይመሽብን እንግባ
ከፌዝ ወከባ
ቀብርና ሲራጥ የጀሀነም ካባ
ለመከላከል ብቃት ለፊትም ለጀርባ
ይጠቅመናልና ወደ ኢስላም እንግባ
እውቃችሁ አሳውቁ
ከማጋራት ራቁ
ብዙም አትሳቁ
ማልቀስ ነው ሐቁ
ይህችን አጭር ገጥም
እንብባችሁም ባይጥም
የጽሑፍ መቋጫ
እንድትመሩበት የጀነትን አቅጣጫ
እንድታመልጡ ከቀብር ፍጥጫ
እንድታከሽፉበት የዘመኑን ወሬ
ለዚህ የገፋፉኝ ትልቁ ችግሬ
እውነት ቦታ ስቶ
ይመለካል ፎቶ
አምላክ ሰው አይመስልም አይመሰልም ከቶ
ሙሴ እንኳን አላየ ማን አነሳው ፎቶ?
ይህ ጉዳይ ይጣራ ባደባባይ ወጥቶ
አስቤ የፃፍኩላችሁ
ወንድማችሁ ይመር
የበዛብኝ ብድር


የአዱንያ ብድር አይከብድም መከፈሉ
አላህ ያበደረኝ ዓይንና ጆሮ አዕምሮ በሙሉ
በማየት በመስማት የትም እንዲውሉ
አልፈጠረምና ጌታችን ጀሊሉ
ገንዘብ አይደለም ዒባዳ ከፈሉ
ማለቱን ሸውቄ አቃተኝ መከፈሉ
ነገ መስካሪ ነው የሰው ልጅ አካሉ
የሰጠንን ፀጋ ዛሬ ነው መከፈሉ
የዒሳም የሙሳም ይኸው ነበር ቃሉ
ሶላታችሁን በርቱ እንዳትታለሉ
ጀነትን ሊያስጡ ገዋይ ይዞራሉ
ተልከው የመጡ ረሆቦት በሙሉ
አንድም ቀን ሳያርፉ ይህን ይመክራሉ
የሙራዳቸውን አይሙላ ጀሊሉ
ያነበባችሁ ሁሉ አሚን አሚን በሉ

## ትዝብት

ከሁሉ በላይ እኔን የገረመኝ
እየተመላለሰ ሁሌ የረበሸኝ
እምነት ከህደት ድርም የነበሩ
ዛሬም ከኛው ጋ ኋላም የሚኖሩ
አዱንያ ያላቸው በሌለው ሲኮሩ
ያልፍልናል ብለው ድሆችም ሲጥሩ
በንብረት ላይ ንብረት ሁሌ ሲጨምሩ
በረኃብ በችግር ሙእሚንን ሲያስቸግሩ
ዱላና እስርን እየቀያየሩ

ከፈርዖን ጀምሮ እስከ ዶርገ ፈጅሩ
ስንዴና ተልባን በገፍ እየዘሩ
አህጉራትን ሁላ በዶላር ሲዞሩ
መንገደኛን እንጂ ሙእሚን መች አከፈሩ
መንገደኛን እንጂ ሙእሚን መች አከፈሩ
አምረው በምድር የደመቁ
እውነት መናሯን ከሰው የደበቁ
በቴክኖሎጂ ጥበብ በጣም የረቀቁ
ስለመዳን ምስጢር ምንም ያላወቁ
የክህደትን ስንቅ ነዋይ ያሰነቁ
ኧረ ተናገሩ ይውጣ እንጂ ሐቁ
ሐቁን ያወቃችሁ አንባቢያን በሙሉ
ለምድራዊ ደስታ እንዳትታለሉ
ሡላችሁ ሳታድሩ ዲኑን ተቀበሉ
ነገ ቧት ቢመጣ የሞትህ መንጠቆ
ከቶ አይቻልም መኖር ተደብቆ
የጌታን አንድነት ልቦናህ አውቆ
የምታገኘው ንዋይ ልብህን አምቆ
የሥጋህም ቀለብ ከምድር ላይ አልቆ
ትጣላለህና ገና ልብስ ወልቆ
የከፈርክለት ገንዘብ እዚህ ላይ ሲቀር
መብላት መጠጣቱ በቀረብህ ነበር
እህቴ ወንድሜ የደረሰህ ዕጣ
በአላህ ተመካ አትክፈር ለቂጣ
አላህ ይጠብቅህ ከቂያማ ቁጣ
ሦስት አምላክ የለም እንደምን ተደርጎ
በማኀበር የሚፈርዱ እንደ ፍርድ ሸንጎ

አዘጋጅ ቀመር ሁሴን
Kemer Husen




አላህ ጌታ ነው!
ኢየሱስ ነቢይ ነው!

# رد المنكرات والشبهات

## بأدلة القرآن والإنجيل والتوراة

(باللغة الأمهرية)


إعداد

قمـــر حسين



الطبعة الثانية

طبعة مصححة منقحة